## ቫሌንቴኒያኖስ ፡ ቀዳማዊ ፡ (፫፻፷፬–፫፻፸፭ ፡ ዓ. ም.) ።

ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ቫሌንቴኒያኖስ ፡ ነገሠ ፤ እሱም ፡ በፈቃዱ ፡ የምዕራቡን ፡ ክፍል፡ ለራሱ ፡ ይዞ ፡ የምሥራቁን ፡ ግዛት ፡ ለወንድሙ ፡ ለቫሌንት ፡ (ቫሌንቱስ) ፡ ሰጠው ። ቫሌንቲኒያኖስ ፡ ጦረኛ ፡ ስለነበረ ፡ በምዕራብ ፡ ከጀርመኖች ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ ያሸ ንፍ ፡ ነበር ። ወንድሙ ፡ ቫሌንት ፡ ግን ፡ መጻሕፍትን ፡ ሃይማኖትን ፡ ከመመርመር፡ በቀር ፤ ጦርነት ፡ አይወድም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ግዛቱን ፡ ከሚያውኩት ፡ ከሑንስና፡ ከጐት ፡ ጋር ፡ ወደፊት ፡ አትግፉ ፡ እንጂ ፡ የያዛችሁትን ፡ መርቄላችኋለሁ ፡ እያለ ፡ አገር ፡ እየለቀቀ ፡ ይታረቅ ፡ ነበር ። በኋላ ፡ ግን ፡ ፈሪ ፡ እየተባለ ፡ ሐሜታ ፡ ስለበዛ በት ፡ እነዚያም ፡ ወደፊት ፡ መግፋትን ፡ ስለአልተዉ ፡ ወታደሩን ፡ ይዞ ፡ ሔዶ ፡ ከወ ራሪዎቹ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ በ፫፻፸፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተና ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ በቫሌንቲያ ኖስ ፡ ፈቃድ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ነገሠ ።

በቫሌንቲኒያኖስና ፡ በወንድሙ ፤ በቫሌንቱስ ፡ ዘመን ፡ የቊስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ መቅዶንዮስ ፡ (ማሴዶንዮስ) ፡ «ዘሠረፀ ፡ እምአብ» ፡ የሚለውን ፡ ይዞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ከአብ ፡ የወጣ ፡ (የተፈጠረ) ፡ ስለሆነ ፡ ከሁለቱ ፡ አካላት ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ያን ሣል ፡ (ሕፁፅ ፡ ነው) ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ስላነሣ ፡ በቊስጥንጥንያ ፡ ጉባዔ ፡ ተደርጎ፡ ነበርና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የሦስቱን ፡ እኩልነት፡ ተከራክሮ ፡ ረታው ። ይኸን ፡ ክርክር ፡ ያገራችን ፡ ጸሐፊዎች ፡ በትልቁ ፡ ቴዎዶስ ዮስ ፡ ዘመን ፡ ያደርጉታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ በ፫፻፸፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በምሥራቅ ፡ ሲነግሥ ፡ መቅዶንዮስ ፡ በ፫፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞቷል ።

## ግራሲያኑስና ፡ ቫሌንቲያኖስ ፡ ፪ኛ ፡ ቀዳማዊ ፡ (፫፻፸፭–፫፻፹፫ ፡ ዓ ፡ ም) ፡

በምዕራብ ፡ ቫለንቴያኖስ ፡ አገሩን ፡ የወረሩትን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጀርመን ፤ ዘሮች ፡ ተዋግቶ ፡ እያሸነፈ ፡ በመጨረሻም ፡ ፈጽሞ ፡ ከጠረፌ ፡ አጠፋለሁ ፡ እያለ ፡ ሲዘጋ ጅና ፡ እነርሱም ፡ ይኸንኑ ፡ ዐውቀው ፡ ለመታረቅ ፡ ውል ፡ ሲደራደሩ ፡ በድንገት፡ በልብ ፡ ሕመም ፡ በ፫፻፸፭ ፡ ሞተ ፡ መንግሥቱንም ፤ ግራሲያኑስ ፡ ቫሌንቲያኖስ ፡ ፪ኛ ፡ የሚባሉት ፡ ሁለት ፡ ልጆቹ ፡ ተካፍለው ፡ ያዙ ። ከነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ ግራሲያ ኖስ ፡ ከልቡ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ወደደ ። በዘመኑ ፡ ቅዱስ ፡ አምብሮዚዮስ ፤ የሚባል ፡ ፭ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ነበር ፡ ግራሲያኑስ ፡ ከርሱ ፡ እየተማከረ፡ ከአለፈው ፡ ጊዜ ፡ የተረፈውን ፡ የአረማውያኑን ፡ ጣዖትና ፡ መቅደስ ፡ አጠፋ ።

በአውግስጦስ ፡ ቄሣር ፡ ጊዜ ፡ በሮማ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ፩ ፡ መቅደስ ፡ ያለው ፡ ትልቅ ፡ የድል ፡ ሐውልት ፡ ተሠርቶ ፡ በዚህ ፡ ሐውልት ፡ በየጊዜው ፡ አማካ ሪዎቹ ፡ ካህናቶቹ ፡ በመሰዊያው ፡ ላይ ፡ ዕጣን ፡ እያጠኑ ፡ ስለትም ፡ መሥዋዕትም ፡ እያደረጉ ፡ በጣም ፡ ያከብሩት ፡ ነበር ፡ ፬ኛው ፡ የክርስቲያን ፡ ዘመን ፡ ሲገመር ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ይፍረስ ፡ አረማውያኑ ፡ አይፍረስ ፡ በመባባል ፡ ትልቅ ፡ ክርክርና ፡ ሁከት ፡ ነበር ። ቈንስጣ ፡ ሁለተኛ ፡ በዘመኑ ፡ ባያፈርሰው ፡ ክብሩና ፡ አምልኮው ፡

እንዲሻር ፡ አዝዞ ፡ ሳለ ፡ ከሐዲው ፡ ዩልያኖስ ፡ መልሶ ፡ አክብሮት ፡ እስከዚህ ፡ ደር ሷል ። ፩ኛው ፡ ባሌንትያኖስም ፡ ይኸንኑ ፡ ክብር ፡ አጸደቀው ። አሁን ፡ ግን ፡ ግራ ሲያኖስና ፡ ቅዱስ ፡ አምብሮስዮስ ፡ ተማክረው ፡ የዚህ ፡ ሐውልት ፡ አምልኮ ፡ በፍ ጹም ፡ እንዲወገድ ፡ አደረጉ ። ሲማክ ፡ የሚባል ፡ የአረማውያኑ ፡ አማካሪ ፡ የሮማ ፡ ከን ቲባ ፡ ይህ ፡ ሐውልት ፡ እንዳይፈርስ ፡ ያደረገው ፡ ክርክርና ፡ ትግል ፡ ብዙ ፡ ነው ። እሱና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ አምብሮሲዮስ ፡ ስለዚህ ፡ ሐውልት ፡ የተመላለሱትና ፡ የተጻጻፉት ፡ ጽሑፍ ፡ ዛሬ ፡ በአንባቢ ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ አለው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ አምብሮሲዮስ ፡ በየጊዜው ፡ የሚነግሡትን ፡ ነገሥታት ፡ በተለይም ፡ የግራስያኑስንና የቴዎዶስዮስን ፡ ድጋፍ ፡ ስላገኘ ፡ በ፫፻፸፪ ፡ ዓ ም ጨርሶ ፡ እንዲፈርስ ፡ አደረገው ።

ግራሲያኑስ ፡ ያረማውያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የአርዮስንም ፡ ትም ህርት ፡ በተቻለው ፡ እንዲጠፋ ፡ አደረገ ፤ በዚህም ፡ ሥራ ፡ የምዕራቡ ፡ ግራሲያኖ ስና ፡ የምሥራቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ተባብረውለት ፡ ነበር ፤ በመጨረሻም ፡ በ፫፻፸፫ ዓ ም ሁለቱም ፡ ቄሣሮች ፡ ተገናኝተው ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በጉባዔ ፡ ተቀምጠው ፡ የጣዖት ፡ አምልኮና ፡ የአርዮስ ፡ ትምህርት ፡ በፍጹም ፡ መሻሩንና ፡ የምሥራቅም ፡ የምዕራ ብም ፡ ዋና ፡ ሃይማኖት ፡ በኒቅያ ፡ ጉባዔ ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ የወሰኑት ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ መርጋቱን ፡ በአዋጅ ፡ አጸደቁ ። ይህ ፡ በሆነበት ፡ ዓመት ፡ በግራሲያኑስ ፡ ላይ ፡ ማክሲም ፡ የሚባል ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ በወታደር ፡ ፈቃድ ፡ ንግሥ ጦርነት ፡ አነሣበት ። ከሱም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደልዮን ፡ ቢሄድ ፡ የዚህ ፡ ከተማ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ገደለው ። ማክሲምም ፡ በ፫፻፸፯ ፡ ከባሌንሲያ ፡ ጋር ፡ ለመተባበር ፡ ሲሞክር አርቦጋስት ፡ የሚባል ፡ የፍራንኮች ፡ ጀኔራል ፡ ገደለው ። ይኸም ፡ ጀኔራል ፡ በምዕ ራብ ፡ አዛዥ ፡ ሲሆን ፡ የግራሲያኑስን ፡ ወንድም ፡ ባሌንሲያኖስን ፡ ፪ኛን ፡ ገደለና ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ለፈቃዱ ፡ የሚውልለትን ፡ ኤውጀኒዮስ ፡ የሚባለውን ፡ ቄሣር ፡ አደረገው ። ይህ ፡ ቄሳር ፡ በግራሲያኖስ ፡ ጊዜ ፡ የወደቀውን ፡ የድል ሐውልት ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ የአረማውያንን ፡ ድጋፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ መልሶ ፡ በምክር ፡ እንደገና ፡ ሊያቆም ፡ ነበር ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ የምሥራቁ ፡ ቄሣር ፡ ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ሰምቶ ፡ ወታደሩን ፡ ይዞ ፡ በግስጋሴ ፡ መጣና ፡ ኤውጀኒዮ ስንና ፡ የጦር ፡ አለቃውን ፡ አርጋቦስትን ፡ በአክሌ ፡ (ኢጣሊያ) ፡ ላይ ፡ አሸነፋ ቸው ፤ በዚህ ፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ የአረማውያን ፡ አምልኮ ፡ የመጨረሻውን ፡ ውድቀት ፡ አገኘ ። በምክር ፡ ቤት ፡ ሊቆም ፡ የነበረው ፡ የድል ፡ ሐውልትም ፡ አማካሪዎቹ ፡ ራሳቸው ፡ ከ፫፻፹፬ ፡ ዓ ም ፡ ዠምሮ ፡ በፍጹም ፡ እንዲ ጠፉ ፡ አደረጉት ።

## ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ (፫፻፸፩–፫፻፹፯ ፡ ዓ ም)—የክርስቲያኖች ፡ መስፋፋትና ፡ የአረማውያን ፡ ዘለቄታ ፡ ውድቀት ።

ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ስለክርስትና ፡ መቋቋም ፤ ስለቀድሞዎቹ ፡ አማልክት ፡ ውድ ቀት ፡ የደከመ ፤ ከቆስጠንጢኖስ ፡ ወዲህ ፡ የተነሣ ፡ ትልቅና ፡ ስሙ ፡ ጥር ፡ ንጉሠ

ነገሥት ፡ ነው ። ዘሩ ፡ ኤስፓኝ ፡ የተወለደው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደኤውሮጳ ፡ ቊጥር በ፫፻፵፯ ፡ (፮ ?) ፡ ዓ ም ፡ ነው ። አባቱ ፡ ጄኔራል ፡ ባሌንሲያኑስ ፡ ይባላል ።

ቴዎዶስዮስ ፡ በግራሲያኑስ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የብሪታንያ ፡ (እንግሊዝ) ፡ ገዥ ፡ ነበር ። ክርስትናን ፡ ተቀብሎ ፡ የተጠመቀው ፡ በ፫፻፹ ፡ ዓ፡ ም፡ ነው ። በዋናው ፡ ቄሣር ፡ በግራሲያኑስ ፡ ፈቃድ ፡ የምሥራቅ ፡ ግፍል ፡ አውግስጦስ ፡ (ንጉሥ) ፡ ተብሎ ፡ ሲያስተዳድር ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፺፬ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ የምዕራቡም ፡ የምሥራቁም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሆነ ።

ቀድሞ ፡ በመዠመሪያው ፡ ግዛቱ ፡ በምሥራቅ ፡ አሁንም ፡ በምዕራቡ ፡ ጭምር ፍራንኮች ፡ ጎቶች ፡ የሚባሉ ፡ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ የጀርመን ፡ ዘሮች ፡ የሮማን ፡ መንግሥት ፡ ለመጣል ፡ የተነሡትን ፡ ሁሉ ፡ ከግማሾቹ ፡ እየተዋጋ ፡ ከቀሩትም ፡ እየታረቀ ደህና ፡ አድርጎ ፡ መንግሥቱን፡ ጠበቀ ። በውስጥ ፡ አስተዳደርና ፡ በፍርድ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የአረማውያኑንም ፡ የአርዮስንም ፡ ትምህርት ፡ በሙሉ ፡ ተቃውሞ ፡ የመላው ፡ ሕዝብና ፡ የመንግሥቱን ፡ ሃይማኖት ፡ በትልቁ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ዘመን ፡ በኒቅያ ፡ ጉባዔ ፡ ፫፻፳፭ ፡ ሊቃውንት ፡ የወሰኑት ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲጸና ፡ አደረገ ።

በርሱ ፡ ዘመን ፡ በአክሱም ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ትልቁ ፡ አብርሃ ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ከካሌብ ፡ በፊት ፡ ዝርዝር ፡ ታሪካቸውን ፡ የማናውቀው ፡ በየሐውልትና ፡ በየገንዘባቸው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ስማቸው ፡ የሚገኘው ፡ እነዋዜብ ፡ እነኡዛስ ፡ ናቸው ።

ግብፅና ፡ ሰሜን ፡ አፍሪካ ፡ ሁሉ ፡ የዚሁ ፡ የታላቅ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ግዛት ፡ ስትሆን ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ እስክንድርያም ፡ ከዚያው ፡ ከቴዎዶስዮስ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ እየተሾመ ፡ ያስተዳድራታል ። በሊቀ ፡ ጵጵስናው ፡ ወንበር ፡ የተቀመጡት ፡ አባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ናቸው ። በሮማ ፡ ወይም ፡ በሚላን ፡ አባ ፡ አምብሮሲዮስ ፤ በቊስጥንጥንያ ፡ አባ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮት ፤ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ የቂሣርያና ፡ የቀጳዶቅያ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፤ ጎርጎርዮስ ፡ ዘኑሲስ ፡ (ኒስ) ፤ ፊልጎስ ፡ ዘኢቆንዮን ፡ (አምፊሎግ ፡ የኢኮኑ) ፡ ቀድሞ ፡ በቊንስጣ ፡ ጊዜ ፡ አርዮሳውያን ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ ሆነው ፡ ሲያሳድዷቸው ፡ እንደነበረና ፡ አሁን ፡ እነዘህ ፡ ሁሉ ፡ ከየተደበቁበት ፡ እየወጡ ፡ በዚሁ ፡ በትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባለሟልና ፡ ስምም ፡ ሆነው ፡ የጣዖታቱንና ፡ የአርዮስን ፡ አማኞች ፡ እየተቃወሙ ፡ የክርስቶስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስፋፉ ፡ እንደነበረ ፡ በዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ ክፍል ፡ ፹፫–፹፬ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ የአረማውያን ፡ አምልኮ ፡ በፍጹም ፡ እንዲቀር ፡ ቤተ ፡ መቅደሳቸው ፡ እንዲዘጋ ፡ ሐውልታቸው ፡ እንዲፈርስ ፤ ለጣዖት ፡ ሲሠዋ ፡ የተገኘ ፡ በሕይወቱ ፡ እንዲቀጣ ፡ በአዋጅ ፡ አስጠነቀቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በምዕራብና ፡ በምሥራቅ ፡ አረማውያን ፡ ላይ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ብዙ ፡ ግፍ ፡ ሠሩባቸው ። መነኮሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ዲያቆናት ፡ በጳጳሳቱና ፡

በኤጲስ ፡ ቆጶሳቱ ፡ መሪነት ፡ ከየበዓታቸው ፡ እየተኸገደገዱ ፡ ወጥተው ፡ የግሪክና ፡ የሮማውያኑ ፡ አማልክት ፡ የነበሩትን ፡ የነዜውስን ፡ (ጁፒቴ ፡) የነአሬስን ፡ (ማርስ) ፡ የሌሎቹንም ፡ ሁሉ ፡ ሐውልትና ፡ ምስል ፡ በዶማ ፡ በመዶሻ ፡ ባገኙት ፡ መጣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ማፈራረስ ፡ በእሳት ፡ ማቃጠል ፡ ያዙ ። ሰዎቹንም ፡ በመያዝ ፡ በመምታት ፡ በማጉላላት ፡ ቀድሞ ፡ በነዲዮቅልጥያኖስ ፡ ጊዜ ፡ አረማውያኑ ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ የፈጸሙትን ፡ አሁን ፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በአረማውያኑ ፡ ላይ ፡ ብድር ፡ መልሰው ፡ አጠቁአቸው ። በቁንስጣ ፡ ጊዜ ፡ ባለሟል ፡ የነበሩት ፡ አርዮሳውያን ፡ ክርስቲያኖች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የስደትና ፡ የመከራ ፡ ዕድላቸው ፡ ከአረማውያኑ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልራቀም ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በእስክንድርያ ፡ በመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ የተቀመጡት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ክርስትናን ፡ ከተቀበሉት ፡ አገረ ፡ ገዥዎችና ፡ የጦር ፡ አለቆች፡ ጋር ፡ እየተባበሩ ፡ በታሕታይና ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ያሉትን ፡ የነፕታህን ፡ የነአሞንን ፡ የነሰራፒስን ፡ አምልኮ ፡ ለመጣል ፡ ተግተው ፡ ይሠሩ ፡ ዠመር ። በሮማና ፡ በቁስጥንጥንያ ፡ እንደሆነው ፡ በዚህም ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በሥልጣን ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በምክርም ፡ በቅጣትም ፡ በመዝረፍም ቢያጠቁዋቸው ፡ በዚህም ፡ ዓይነት ፡ የክርስቲያኑ ፡ ቊጥር ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ፡ መበርከቱ ፡ ባይቀር ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ለቀድሞው ፡ አምልክና ፡ ልማድ ፡ የቀኑት ፡ በነፕላቶን ፡ ፍልስፍና ፡ የበሰሉት ፡ በዘመኑ ፡ በግሪክና ፡ በኮፕት ፡ ቋንቋና ፡ ጽሑፍ ፡ የሰለጠኑት ፡ ግብፆችና ፡ ግሪኮች ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ጽርዓዊና ፡ ግብፃዊ፡ሃይማኖት ፡ ለውጠው ፡ ከእስራኤል ፡ የመነጨውን ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ መቀበል ፡ እንደክህደት ፡ ስለቆጠሩት ፡ አጥብቀው ፡ መከላከልን ፡ መረጡ ። ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡ አርጌንስ ፡ ክርስትናን ፡ ከነፕላቶን ፡ ትምህርት ፡ ጋር ፡ ማመሳሰልና ፡ ማዋሐድ ፡ እንደሞከረው ፡ ዓይነት ፡ የግብፅና ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ በእስክንድርያ ፡ ያሉት ፡ የግሪክ ፡ ሕዝብ ፡ የቀድሞውን ፡ የነአሞንን ፡ አምልኮ ፡ ከክርስትና ፡ ጋር ፡ እያቀላቀሉ ፡ ባንድነት ፡ ይዘው ፡ የነዚያን ፡ ልማድና ፡ ወግ ፡ ካዲሱ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ከወጉና ፡ ከሥርዓቱ፡ ጋር ፡ እያደባለቁ ፡ ይይዙ ፡ ዠመር ።

ቅጣትና ፡ ስደት ፡ የፈሩት ፡ ወገኖች ፡ በስም ፡ ክርስቲያን ፡ እየተባሉ ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ የነአሞን የነሰራፒስ ፡ በዓል ፡ በሚውልበት ፡ ቀን ፡ አብረው ፡ እየዋሉ ፡ የነዚያን ፡ የመሥዋዕትና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ወግ ፡ መከፈል ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ዠመር ። የዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱንና ፡ የክርስቲያን ፡ አገረ ፡ ገዥዎቹን ፡ ስለአላስደሰታቸው ፡ በየጊዜው ፡ ግጭትና ፡ ጦርነት ፡ ተደረገ ። በነዚሁ ፡ መካከል ፡ ከቀድሞው ፡ ሃይማኖት ፡ በፍጹም ፡ ያልተለወጡት ፡ አዲሱን ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ በይፋ ፡ የሚቃወሙ ፡ አሉ ። በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ በሮማና ፡ በምሥ

ራቅ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ እንደሆነው ፡ በዚህም ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ በእስክንድርያ ፡ ብዙ ፡ ሁከትና ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ ተደረገ ።

ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ በክርስቲያኖቹና ፡ በቀድሞዎቹ ፡ አማልክት ፡ ተከታዮች፡ መከከል ፡ ጦርነት ፡ የተደረገው ፡ ከ፫፻፹፯–፫፻፺፩ ፡ ዓ ም ድረስ ፡ የእስክንድርያን፡ የሊቀ፡ጳጳስነት፡ሥልጣን፡ አባ ፡ ቴዎፍሎስ፡ በያዙበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ሊቀ፡ ጳጳሱ ፡ አባ፡ቴዎፍሎስ ፡ አረማውያኑ፡በምክርና ፡ በተግሣፅ ፡ አለመለወጣቸውን ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ የአማልክቱን ፡ ቤት ፡ መቅደስ ፡ ለማፍረስ ፡ አምልኮውን ፡ ጨርሶ፡ለማጥፋት፡ ከልብ ፡ ስለተነሡበት ፡ በቁጣ ፡ መነኮሳቱን ፡ ቀሳውስቱን ፡ ዲያቆናቱን፡ በክርስትና ፡ ያመነውን ፡ ሁሉ ፡ አስከትለው ፡ ዋናው ፡ የሰራፒስ ፡ የጣዖት ፡ መቅደስ ፡ ወዳለበት ፡ መኀሪያቸውን ፡ እየያዙ ፡ ሄዱ ። ለቀድሞው ፡ አምልኮ ፡ ቀና ዕያን ፡ የሆኑት ፡ ወገኖች ፡ ግብፆችና ፡ ግሪኮቹ ፡ መቅደሳቸው ፡ እንዳይፈርስ፡ ለመከላከል ፡ ተዘጋጅተው ፡ ይጠባበቁ ፡ ዠመር ። የነሱም ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ መሪ ዎች ፡ ፈላስፋው ፡ ኦሊምፒዮስ ፤ ሌሎችም ፡ ሄላንድና ፡ አሞን ፡ (በአምላኩ ፡ ስም ፡ የሚጠራው) ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ቅጥር ፡ ከውስጥ ፡ መሽገው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በጦርነት ፡ ከተከላከሉ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱና ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ባገረ ፡ ገዥውና ፡ በወታደሮቹ ፡ የተደገፉ ፡ ስለሆኑ ፡ ክርስቶስን ፡ ያልተቀበሉት ፡ መሸነፍ ፡ ግዴታ ፡ ሆነባቸው ።

ስለዚህ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ መነኮሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ዲያቆናትና ፡ ወታደ ሮች ቅጥሩን ፡ ጥሰው ፡ እየተንጋጉ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ የቤተ ፡ መቅ ደሱን ፡ መዝጊያ፡እየፈነቃቀሉ ፡ ሐውልቶቹንና፡ምስሎቹን ፡ እየገለባበጡ ፡ ሰባብረው ፡ በውስጡና ፡ በዙሪያው ፡ የተገኘውን ፡ ሀብት ፡ ዘረፉት ። በዚህ ፡ ቀን ፡ በሰራ ፒስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ ታናናሽና ፡ ታላላቅ ፡ ሐውልቶች ፡ ተሰባ በሩ ፡ ይባላል ። ጥናት ፡ ስለጥንታዊው ፡ እስክንድርያ በሚል ፡ አርኢስት ፡ አሌክ ሳንድር ፡ ማስክ ፡ ደ ፡ ዘጌብ ፡ የጻፈውን ፡ ፩፻፳–፪፻፳፱ ፡ ገጽ ፡ ተመልከት ።

በዚህ ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ በጥንታዊው ፡ የግብፅ ፡ ፊደል ፡ (ሂዬሮግሊፍ ፡) በተ ሻሻለው ፡ (በዴሞቲክ) ፡ እንደዚሁ ፡ የግሪክና ፡ የግብፅ ፡ ቅይጥ ፡ ጽሑፍና ፡ ቋንቋ ፡ በሆነው ፡ በኮፕት ፤ በግሪክና ፡ በሮማይስጥ ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡ ያሉበት ፡ ታላቅ ፡ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በአባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቃጠለ ። ክርስቲያኖቹም ፡ የሚቃወሙት ፡ የግብፅን ፡ አማልክትና ፡ አምልኮ ፡ ብቻ ፡ አል ነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ የአይሁድን ፡ የግሪኮቹን ፡ የነዜውስን ፡ አምልኮ ፡ የነፕላ ቶንን ፡ ትምህርት ፡ የአርዮስንም ፡ አሳብ ፡ ጭምር ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ዛሬ ፡ ለታሪክ ፡ ምርመራና ፡ ዕውቀት ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ሊሰጥ ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ ይህ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በመቃጠሉ ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንት ፡ ሁሉ፡ በአባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ያዝናሉ ። ከዚያ ፡ የቀረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ በዐ ረቦች ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ የተቃጠለውን ፡ ወደፊት ፡ እናንባለን ።

ከአባ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ቀጥለው ፡ በተሾሙት ፡ በአባ ፡ ቄርሎስ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ዘመን በዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በክርስቶስ ፡ ያላመኑትን ፡ በሚያበርሩበት ፡ ጊዜ የማቴማቲሲያኑ ፡ የቴዎን ፡ (Theon) ልጅ ፡ ሂፓቲያ ፡ (Hypatia) የምትባል ፡ የምታምር ፡ ቆንጆ ፡ ወጣት ፤ በግሪክ ፡ ፍልስፍና ፡ የሰለጠነች ፡ የሖሜርን ፡ ድርሰቶች ፡ በቃሏ ፡ የምትተረጉም ፡ ነበረች ። ይህች ፡ ወጣት ፡ ገና ፡ በክርስትና ፡ ያላመነች ፡ ከመሆኗ ፡ ጋር ፡ የፕላቶንንና ፡ የአሪስቶትን ፡ (የአፍላጦንና ፡ የአርስጣጣሊስን ፡ ) ትምህርት ፡ ማስተማር ፡ ከኃጢአት ፡ ተቆጥሮባት ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ በአባ ፡ ቄርሎስና ፡ በአገረ ፡ ገዥው ፡ በኦሬስቴስ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ እንዳይኖር ፡ የምታደርግ ፡ ናት ፡ ተብላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በሰረገላ ፡ ስትሄድ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ከሰረገላ ፡ ጐትተው ፡ አውርደው ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያዳፉ ፡ ወስደው ፡ ልብሷን ፡ እየቀደዱ ፡ ሰውነቷን ፡ በባልጭት ፡ እየበጡ ፡ አሰቃይተው ፡ ገደሏት ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ (፫፻፺-፬፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ) ፡ ከክርስትና ፡ ውጭ ፡ የቀድሞ ፡ የአማልክት ፡ ሃይማኖት ፡ በያዘው ፡ በግብፅና ፡ በግሪክ ፡ በሌላውም ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ሥልጣን ፡ በደረሰበት ፡ ወገን ፡ በሮማና ፡ በምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ መከራና ፡ ስደት ፡ ወረደባቸው ። ጠላቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ ክፉ ፡ ለሚያደርጉባችሁ ፡ጸልዩ ፡ ያለው ፡ አምላካዊ ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አልተፈጸመም ። ነገር ፡ ግን ፡ አረማውያኑ ፡ በንዲዮቅልጥያኖስ ፡ ዘመን ፡ ያሰዩዋቸውን ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡ ባሁኑ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ በሆኑት ፡ በነታላቅ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያኖቹ ፤ መልሰው ፡ አሳዩዋቸው ። እነቴዎዶስዮስ ፡ እነመርቅያን ፡ ከአገረ ፡ ገዦዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ስለደገፉዋቸው ፡ ሥራቸው ፡ ከክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ከርኅራኄውና ፡ ከይቅርታው ፡ ውጭ ፡ ቢሆንም ፡ ጳጳሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ዛሬ ፡ በፋንታቸው ፡ አጥቂዎች ፡ ሆነው ፡ በኃይልም ፡ በማስተማርም ፡ የክርስቲያን ፡ ቍጥር ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ ። ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ጳጳሳትም ፡ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ በብዙ ፡ ይገቡ ፡ ዠመር ። እንዲያውም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ያላመኑትን ፡ ለማሳመን ፡ እንዲመቻቸው ፡ በመላው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መፈራትንና ፡ መከበርን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ በሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሥልጣናቸው ፡ ላይ ፡ ያገረ ፡ ገዥነቱን ፡ ሥልጣን ፡ እየደረቡ ፡ እስከ ፡ መያዝ ፡ ወታደሩን ፡ በቀጥታ ፡ እስከ ፡ ማዘዝ ፡ ደርሰዋል ።

የጥታህና ፡ የሰራፒስ ፡ አምልኮ ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲወድቅ ፡ የአሞን ፡ አምልኮ ፡ በገነነበት ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ በቴብ ፡ ከተማ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ይህችን ፡ የደመቀች ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፤ በፊት ፡ የአሶራውያን ፡ ጦር ፡ ከአንሳቆላት ፡ በኋላ ፡ የፋርስ ፡ ጦር ፡ በንጉሡ ፡ በካምቢዝ ፡ መሪነት ፡ ከተማዋን ፡ በኃይል ፡ ይዞ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፳፭-፭፻፳፪ ፡ ዓመት ላይ ፡ ፍርስርሷን ፡ አውጥቶ ፡ አጥፍቷት ፡ ነበር ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በዕውቀትና ፡ በፍልስፍና ፡ የበሰሉት ፡ ግሪኮቹ ፡ እነበጥሊሞስ ፡ መልሰው ፡ እያቃኑ ፡ ሠርተው ፡ አቋቁመው ፡

አምልክአቸውን ፡ ከአገር ፡ ተወላጁ ፡ አምልክ ፡ ጋር ፡ በማመሳሰል ፡ አዋህደው ፡
በ ፡ «አሞን – ዜውስ» ፡ እያመኑ ፡ በሰላም ፡ ኖሩ ። በነሱ ፡ እግር ፡ የተተኩት ፡
ሮማውያንም ፡ ‹አሞን – ጁፒቬ» ፡ ወይም– ‹አሞን ፡ ጌፒተር› ፡ እያሉ ፡ ያለ
ፈውን ፡ የሕዝቡን ፡ መቅደስ ፡ ሳያፈርሱ ፡ አምልክውንም ፡ ሳይሽሩ ፡ እንዲያውም
በቀድሞው ፡ የአማልክት ፡ መቅደስ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እነሱ ፡ አዳዲስ ፡ ሥራ ፡ በየ
ጊዜው ፡ እየጨማመሩ ፡ በክብሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሲያደርጉ ፡ ሕዝቡም ፡ እንደተለ
መደ ፡ በዓሉን እያከበረ ፡ ገዥዎችና ፡ ተገዥዎች ፡ ተስማምተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር።
ክክርስትና ፡ ወዲህ ፡ በታሕታይ ፡ ግብፅ ፡ ይልቁንም ፡ ከመምፊስ ፡ ወዲህ ፡ እስክ
ንድር ፡ የመሠረታት ፡ ከተማ ፡ እስክንድርያ ፡ እየደመቀች ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ ቊጥር
እየበረከተ ፡ የሊቃነ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሥልጣን ፡ እየገነነ ፡ ሲሄድ ፡ በዚያ ፡ የነበረ
ውን ፡ ሰራፒስ ፡ (ሶር–አፒስ)–የማበለውን ፡ ግብፆቹም ፡ ግሪኮቹም ፡ በሕብረት ፡
የሚያመልኩትን ፡ ጣዖት ፡ ሽረው ፡ መቅደሱን ፡ እንዳፈረሱት ፡ ሁሉ ፡ የእስክንድርያ ፡
ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የሊቃነ ፡ ጵጵስናቸው ፡ ሥልጣን ፡ እስከ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡
እስከ ፡ ቴባዩድ ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ናፓታ ፡ ሲዘረጋ ፡ መነኮሳቱና ፡ ቀሳውስቱ ፡
ከቁስጥንጥንያ ፡ ነገሥታት ፡ ከነቴዎዶስዮስ ፡ ከነመርቅያን ፡ (ማርቺያኑስ ፡) እየተ
ሾሙ ፡ ከሚላኩት ፡ የክርስቲያን ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ ጋር ፡ እየተባበሩ ፡ በቴብ ፡
ከተማና ፡ በቴባይድ ፡ አውራጃ ፡ ያለውን ፡ የአሞንን ፡ አምልክ ፡ ለማጥፋት ፡
በተቻላቸው ፡ ሞከሩ ።

ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ (፬፻–፭፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት) ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በ፫፻ና ፡
በ፬፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ከታሕታይ ፡ ግብፅና ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡
ግዛት ፡ እየተሰደዱ ፡ ወደ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ በረሀ ፡ እየመጡ ፡ በብሕትውና ፡
የሚኖሩት ፡ ያንድ ፡ በሕርይና ፡ የተዋሕዶ ፡ ወገኖች ፡ አባ ፡ ጳውሊ ፡ (የመጀመሪያው ፡
የክርስቲያን ፡ ባሕታዊ) ፡ ቀጥሎ ፡ የርሳቸው ፡ ደቀ ፡ መዝሙርና ፡ ተከታይ ፡ አባ ፡
እንጦንዮስ ፡ (የበረሀው ፡ ኮከብ ፡ ተብለው ፡ የተሰየሙት) ፤ የርሳቸው ፡ ተከታይ ፡
አባ ፡ ጳኵሚስ ፡ አባ ፡ ቀኑዳ ፤ አባ ፡ ሙሴ ፡ ሌሎችም ፡ መነኰሳት ፡ በአስቄ
ጥስና ፡ በሌላውም ፡ ሥፍራ ፡ ገዳም ፡ እየገደሙ ፡ ተከታይ ፡ እያበረከቱ ፡ በኃይ
ልም ፡ ባይሆን ፡ በድካም ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ይኸን ፡ ዓለም ፡ በመናቅ ፡ (በም
ናኔ ፡ በብሕትውና) ፡ በጸሎትና ፡ በማስተማር ፡ በበጎ ፡ ተግባርና ፡ በመልከም ፡
አርአያ ፡ የአሞንን ፡ አምልክ ፡ ሲገዘግዙት ፡ ቆይተዋል ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡
በቴባይድ ፡ አምላክ ፡ በአሞን ፡ ስም ፡ የተሠየሙ ፡ አባ ፡ አሞን ፡ የሚባሉት ፡ ከሌ
ሎች ፡ አበው ፡ መነኰሳት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ስመ ፡ ሞግሼያቸው ፡ የሆነውን ፡
የአሞንን ፡ አምልክ ፡ ለመጣል ፡ ሠርተዋል ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ በነዚህ ፡ መነኰ
ሳት ፡ አበው ፡ የተመሠረተው ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ የሚባለው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
የባሕታውያን ፡ የመነኰሳት ፡ መደብ ፡ ሆኖ ፡ የገዳምነት ፡ ሥራውን ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ይቀጥላል ።

የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ መነኰሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ የሠሩት ፡
ሥራ ፡ ገድልና ፡ ትሩፋታቸው ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ታሪክ ፡ በዓ

ረብኛ ፡ ተጽፎ ፡ የቆየው ፡ በዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከዓረብኛ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተተርጕሞ ፡ በገራችን ፡ ይገኛል ። ስሙ ፡ በግዕዝኛ ፡ „መጽሐፈ ፡ ገነት ፤ ገድለ አበው ወይም ዜና አበው ፡ ቅዱሳን„ ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የመነኮሳቱ ፡ ብሕትውና ፡ አገልግሎት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንፈሳዊ ፡ አነጋገር ፡ ሲቀረጽ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አማልክቱን ፡ መቃወማቸው ፡ እምብዛም ፡ በዝርዝር ፡ ባይገኝ ፡ በሚያደርጉት ፡ መንፈሳዊ ፡ ተጋድሎ ፡ እነዚህ ፡ መነኰሳት ፡ የቀድሞውን ፡ አምልኮ ፡ ለማጥፋት ፡ ሲጣጣሩ ፡ ቆይተው ፡ የነበረውን ፡ ከቴዎዶስዮስ ፡ አዋጅ ፡ ወዲህ ፡ ከእስክንድርያ ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ቴባይድ ፡ (ላዕላይ ፡ ግብፅ) ፡ የመጡት ፡ የክርስቲያን ፡ አገረ ፡ ገዥዎችና ፡ ወታደሮች ፡ መነኰሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ በግድም በውድም ፡ እያደረጉ ፡ በቅጣት ፡ በውርስ ፡ እያስፈራሩ ፡ የአሞን ፡ አምልኮ ፡ ጨርሶ ፡ እንዲጠፋ ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲስፋፋ ፡ አደረጉ ። ከነዚህም ፡ መከከል ፡ እላይ ፡ ስማቸውን ፡ የጠቀስናቸው ፡ አባ ፡ ቀኑዳና ፡ አባ ፡ ሙሴ ፡ የጣዖታቱን ፡ ሐውልት ፡ የቴዎዶስዮስን ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ በማፍረስ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ናቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ የለመዳቸውንና ፡ የሚወዳቸውን ፡ አማልክት ፡ የአማልክቱ ፡ በዓል ፡ በሚውልበት ፡ ቀን ፡ በወግ ፡ በሥርዓት ፡ በስብሰባ ፡ በዙረት ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ መሥዋዕትና ፡ ድግስ ፡ የሚያደርገውን ፡ የደስታ ፡ በዓል ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመተው ፡ ከልቡ ፡ ስለተቸገረ ፡ በትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በአባ ፡ ቴዎፍሎስና ፡ በአባ ፡ ቄርሎስ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ዘመን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አዋጅና ፡ ቅጣት ፡ ቢያፈራርቁበትም ፡ ጨርሶ ፡ ሊተው ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ግማሹ ፡ አዲሱን ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብሎ ፡ ሲዘር ፤ የቀረው ፡ እምቢ ፡ እያለ ፡ ቅጣቱን ፡ እየቻለ ፡ በዚያው ፡ ጸና ። ግማሹ ፡ ደግሞ ፡ ከልቡም ፡ ይሁን ፡ ከአፍ ፡ ክርስትናን ፡ በጥምቀት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ የክርስትናን ፡ ሥርዓት ፡ ከአረማውያኑ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ አደባልቆ ፡ ይዞ ፡ ይኖር ፡ ዠመር ። ግሪኮቹ ፡ አሞን ፡ ማለት ፡ ዘውስ ፡ ነው ፡ እንዳሉ ፡ እነዚህ ፡ ክርስትናን ፡ በመጀመሪያ ፡ የተቀበሉትና ፡ የቀድሞውን ፡ ለመተው ፡ የተቸገሩት ፡ አሞን ፡ ማለት ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ ለማዘንበል ፡ ፈለጉ ። ይኸውም ፡ ዛሬ ፡ በንዳንድ ፡ መንደርና ፡ ባላገር ፡ ክርስቲያኖች ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ ከስቀደሱ ፡ በኋላ ፡ ወደመንደር ፡ ሲመለሱ ፡ ለግንቦት ፡ ልደታ ፡ አድባር ፡ ከሚባለው ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ተቀምጠው ፡ ቡና ፡ አፍልተው ፡ ቆሎ ፡ ቆልተው ፡ ከጣዖት ፡ አምልኮ ፡ የመነጨውን ፡ የበረንትቻ ፡ በዓል ፡ እንደሚያከብሩት ፡ ወይም ፡ አድባሯ ፡ ማርያም ፡ ነች ፡ እንደሚሉት ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

እንደዚሁም ፡ ዛሬ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ በገጠማቸው ፡ ጊዜ ፡ ለታቦት ፡ ከተሳሉ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩ ፡ ሊከናወን ፡ መቻል ፡ አለመቻሉን ፡

ከቃልቻ ፡ እንደሚጠይቁት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያንነታቸውን ፡ በጥምቀት ከገለጹ ፡ በስሙም ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞውን ፡ ያረማዊ ፡ በዓላቸውንና ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይከተሉ ፡ ዠመር ። በዚህ ፡ አወላዋይ ፡ ሁኔታ ፡ የግብፅና ፡ የግሪክ ፡ የሌላውም ፡ አገር ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ የክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ አጋማሹ ፡ ሲኖር ፡ የቀረው ፡ ከልቡ ፡ ክርስትናን ፡ ተቀብሎ ፡ በሰላም ፡ ሲኖር ፡ የቀረው ፡ በእምቢታ ፡ የቀድሞውን ፡ እንደያዘ ፡ በዚሁ ፡ በግትርነቱ ፡ ሲቀጣ ፡ ሲወረስ ፡ ሲጎጠጥ ፡ ከ፬ኛው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ያለውን ፡ ጊዜ ፡ አሳለፈ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የአሳብና ፡ የሃይማኖት ፡ ነፃነት ፡ በሌለበት ፡ በዚያን ፡ ዘመን፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ መሪ ፡ የደገፈው ፡ ነገር ፡ ምንም ቢሆን ፡ መስፋፋቱ ፡ አይቀርምና ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ነገሥታት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በሕብረት ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ በታሕታይና ፡ በላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ እንደዚሁም ፡ በኑብያ ፡ (ሱዳን) ፡ የጥንቱን ፡ የግብፆች ፡ አማልክት ፡ የነአሞንን፡ የነኦሲሪስን ፡ የነፕታህን ፡ የነአፒስን ፡ ግሪኮቹ ፡ አምጥተው ፡ የደረቡትን ፡ የነአጵሎንን ፡ እምነት፡ እያደር ፡ ለመጣል ፡ በትጋት ፡ እየሠሩ ፡ ለማጥፋት ፡ በተቃረቡበት ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞው ፡ የነአሞን ፡ አምልኮ ፡ ጨርሶ ፡ ለመጥፋት ፡ ደንገዝገዝ ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፸ ዓ ፡ ም ፡ በመካ ፡ መዲና ፡ መሐመድ ፡ ተወለደ ። እርሱም ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ የእስልምናን ፡ ሃይማኖት ፡ በፋንታው ፡ ወለደ ።

የዚህንም ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ እስክናገኘው ፡ ድረስ ፡ አሁን ፡ ወደቴዎዶስዮስ ፡ ታሪክ ፡ እንመለስ ።

ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናዒ ፡ ሆኖ ፡ ያለፉት ፡ ነገሥታት ፡ በቸልታ ፡ ወይም ፡ በትዕግሥት ፡ ያቆዩትን ፡ የአረማውያንን ፡ ሃይማኖት ፡ በፍጹም ፡ እንዲጠፋ ፡ በማድረጉ ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የእስክንድርያና ፡ የኢትዮጵያም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጻድቅ ፡ ቅዱስ ፡ እያሉ ፡ ያመሰግኑታል ።

የዮሐንስ ፡ መደብር ፡ መጽሐፍ ፡ በ፹፫ኛው ፡ ክፍል ፡ «ታኦዶስዮስ ፡ ንጉሥ፡ መፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር» ፡ እያለ ፡ ደጋግሞ ፡ ያነሣዋል ። በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተካፍሎ ፡ የምዕራቡን ፡ ክፍል ፡ ይገዛ ፡ የነበረውን ፡ ግራስያኑስ ፡ ቂሣርን ፡ ጨምሮ ፡ አብሮ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ በምሥጋና ፡ ያነሣቸዋል ፡ "ወእሉ፡ እሙንቱ ፡ አግራድያኖስ ፡ ወታኦዶስዮስ ፡ (ግራሲያኑስና ፡ ቴዎዶስዮስ) ፡ ነገሥት ፡ እሙራን ፡ ቅኑያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገብሩ ፡ ሠናያተ ፡ በትግሐት .... "

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ምሥጋናው ፡ ቢበዛም ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትና ፡ በቅርቡ ፡ የነበረው ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ሳይቀር ፡ የገቡበትን ፡ በከንቱ ፡ ነፍስ ፡ የማስገደልን ፡ ኃጢአት ፡ እርሱም ፡ ሳይገባበት ፡ አልቀረም ። የርሱ ፡ ወታደሮችና ፡ አርዮሳውን ፡ በተሰሎንቄ ፡ በዚሁ ፡ በሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ሲጣሉ ፡ ሲከራከሩ ፡ የነበሩት ፡ እያደር ፡ ጠቡ ፡ ከሮ ፡ ነበርና፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ፈቃድ ፡ ወታደሮቹ ፡ ሰባት ፡ ሺ ፡ አርዮሳውያን ፡ ገደሉ ፡ ይባላል ።

ይህ ፡ በሆነበት ፡ ዓመት ፡ ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሳለም ፡ ከኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ከአባ ፡ አምብሮስዮስም ፡ ለመገናኘት ፡ መጣ ። ወደቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ሄዶ ፡ ቅጥሩን ፡ ገብቶ ፡ እቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ ሲደርስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ „ኃጢአት ፡ በመሥራት ፡ ዳዊትን ፡ መስለኸዋል ፡ በል ፡ በንስሐም ፡ ምሰለው" ፡ ሲል ፡ ወደውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ ከበ ራፉ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ አገደው ። ቴዎዶስዮስም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ መንፈሱ ፡ ተወቅሶ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ ተመልሶ ፡ ፰ ፡ ወር ፡ ሱባዔ ፡ ገብቶ ፡ ከጸለየ ፡ በኋላ፡ በኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደልቡ ፡ ይገባ ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ ወደሥፍራው ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ተመልሶ ፡ በ፫፻፺፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተ ፤ መንግሥቱንም ፡ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ አርቃድዮስና ፡ አኖሬዎስ ፡ ተከፈሉት ።

በሮም ፡ (ቁስጥንጥንያ) ፡ መንግሥት ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ ታላቁ ፡ ቴዎዶስዮስና ፡ ደግሞ ፡ የልጁ ፡ የአርቃድዮስ ፡ ልጅ ፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ አሉ ፤ የሁለቱ ፡ የግ ዛት ፡ ጊዜና ፡ ሥራ ፡ ሳይለይ ፡ ስንክሳርና ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ የቴዎዶስዮስን ፡ ስም ፡ በምሥጋና ፡ ያነሳል ፡ አባ ፡ ኪሮስንም ፡ የገዳመ ፡ አስቂጥሱንና ፡ አባ ፡ ፓምዋ ፡ (ፓምቦ) ፡ የቴዎዶስዮስ ፡ ወንድሞች ፡ ሲያደርጋቸው ፡ የየትኛው ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ መሆ ኑን ፡ አይለይም ። እንደዚሁም ፡ የገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ገድል ፡ „ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሠ ፡ ቁስጥንጥንያ» ፡ ሲል ፡ የየትኛው ፡ መሆኑ ፡ አልተገለ ጸም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸን ፡ እንለፍና ፡ ወደዋናው ፡ ጉዳይ ፡ እንመለስ ።

## አኖርዮስ ፡ (ሖኖሪዩስ)ና ፡ አርቃድዮስ ፡ (አርካዲዩስ) (፫፻፺፭–፬፻፰ዓ. ም.) ።

ትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ሲሞት ፡ እንደተናዘዘው ፡ አኖርዮስ ፡ የምዕራቡን ፡ አርቃድ ዮስ ፡ የምሥራቁን ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ጀመር ። የሮማ ፡ ግዛት ፡ የምዕራብና ፡ የምሥራቅ ፡ ግዛት ፡ እየተባለ ፡ መጠራት ፡ ከጀመረ ፡ ብዙ ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ቄሣር ፡ እንደ ፡ ቆስጠንጢኖስም ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ቄሣር ፡ ይመራል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ሁለት ፡ ግዛት ፡ ለየብቻው፡አልተለየም ። አሁን ፡ ግን ፡ በነዚህ ፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ልጆች ፡ በአኖርዮስና ፡ በአርቃድዮስ ፡ ጊዜ መከፈል ፡ ጀምሮ ፡ ከአኖርዮስ ፡ ቫሌንቲንያን ፡ ከዚያ ፡ ሮሙ ሉስ ፡ አውጉስቱስ ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ የምዕራቡ ፡ እስከ ፡ ሮሙሉስ ፡ አውጉስቱስ ፡ (፬፻፸፮ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ቆይቶ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀጥሎ ፡ ከሰሜን ፡ የወረዱ ፡ የጐት ፡ የአስ ትሮጎት ፡ የቪዚጎት ፡ የቫንዳል ፡ የሁንስ ፡ የፍራንክ ፡ የጀርመን ፡ የአንግሎ ፡ ሳክሰንና ፡ የሞንጎል ፡ ዘሮች ፡ በየጊዜው ፡ እየወጉ ፡ ከአስቸገሩት ፡ በኋላ ፡ መጨረሻውን ፡ ጣሉ ትና ፤ በያለበት ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቆሙ ። ከነዚያ ፡ ዘር ፡ የወረደው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ መንግሥቱን ፡ይዞ፡ ይገኛል።ይኸውም፡አንግሎ፡ሳክሰን፡የሚባሉት፡በእንግሊዝ፤ በጀርመን፤ ፍራንክ ፡ በፈረንሳዊ ፤ ዊዚጎት ፡ የኤስፓኝን ፤ አስትሮጎት ፡ ሎጎምባርድ ፡ በኢጣሊያን ፡ አገር ፡ ላይ ፡ እየተመሠረቱ ፡ ቀደሞ ፡ በነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እየተጨመሩ ፡ መንግ

ሥታቸውን ፡ አቋቋሙ ። የምሥራቁ ፡ የሮማ ፡ ግዛት ፡ ግን ፡ ከአርቃድዮስ ፡ ዠምሮ ፡ (፫፻፺፭ ፡) ፩ሺ፫፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ቱርኮች ፡ በ፲፭ ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላይ ፡ ጣሉት ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የምዕራቡን ፡ ወገን ፡ ትተን ፡ ከአገራችን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ በሃይማኖትም ፡ በጽሑፍም ፡ በአስተዳደርም ፡ በጠ ቅላላው ፡ በሥልጣኔ ፡ ግንኙነት ፡ ያለውን ፡ የምሥራቁን ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ እንጽፋለን ፡ ይኸም ፡ ግዛት ፡ የትንሹ ፡ ሮም ፡ የቈስንጥንጥንያ ፡ (ቢዛንስ) ፡ ግዛት ፡ የሚባለው ፡ ነው ። ዋናውም ፡ ከተማ ፡ ዛሬ ፡ ቱርኮች ፡ ይዘው ፡ ስታንቡል ፡ የሚሉት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በመሥራቹ ፡ በቆስጠንጢኖስ ፡ ስም ፡ ቈስጥንጥንያ ፡ የሚባለው ፡ ነው ። አርቃድዮስ ፡ የምሥራቅ ፡ ንጉሥ ፡ እየተባለ ፡ ከ፫፻፺፭ ፡ እስከ ፡ ፬፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ሲገዛ ፡ ጠባዩ ፡ ደካማ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በመኳንንቱና ፡ ይልቁንም ፡ በሚ ስቱ ፡ በአውዶቅስያ ፡ ይመራ ፡ ነበር ። አወዶቅስያ ፡ ጌጣ ፡ ጌጥ ፡ የምታፈቅር ፡ ሥል ጣንን ፡ መፈራትን ፡ መከበርን ፡ የምትወድ ፡ ኃይለኛ ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ በኃጢአቷና ፡ የአርዮስን ፡ ትምህርት ፡ ከመውደዷ ፡ የተነሣ ፡ ከቈስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከአባ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ (ክሪሶስቶም ፡) ጋር ፡ የነበራቸው ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ በግዞት ፡ አሣሥራ ፡ በበኋ ፡ ላይ ፡ ሥል ጣኗን ፡ እያሳየች ፡ ስትኖር ፡ በ፬፻፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተች ። በኋላም ፡ አርቃድዮስ ፡ በ፬ ፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተ ። በአርቃድዮስ ፡ ዘመን ፡ የቈስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የነበ ረው ፡ እላይ ፡ ስሙን ፡ የጠቀስነው ፡ የዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ድርሳኑ ፡ በአገራ ችን ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ እንደዚሁም ፡ ስለርሱ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ በምዕ ራፍ ፡ ፳፰ ፡ በሰፈው ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፏል ።

ዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ (፬፻፰–፬፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡) የንስጥሮስና ፡
<u>የአባ ፡ ቄርሎስ ፡ ክርክር ።</u>

አርቃድዮስ ፡ ሲሞት ፡ ልጁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዳግማዊ ፡ ነገሠ ። እንደ ፡ ነገሠ ፡ ቈስጥንጥንያን ፡ ከጠላት ፡ የሚከላከልበት ፡ ያሠራው ፡ ቅጥር ፡ በዘመኑ ፡ ስለፍርድ ፡ ያዘጋጀው ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ (ኮድ) ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ አድርጎታል ። እንደዚሁም ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በየሰዓቱ ፡ ጸሎት ፡ መዝሙር ፡ ቅዳሴ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ሚደረግ ፡ የርሱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ገዳም ፡ ሊቆጠር ፡ ምንም ፡ አልቀረ ውም ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

በርሱ ፡ ዘመን ፡ የቈስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የነበረው ፡ አባ ፡ ንስጥሮስ ፡ (ኔስቶሪዮስ ፡) ለክርስቶስ ፡ ሰውነታዊና ፡ መለኮታዊ ፡ የሆኑ ፡ የተለያዩ ፡ ሁለት ፡ አካላት ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፡ ስለ ፡ አሉት ፡ በሰውነቱ ፡ ከአብ ፡ አይወለድምና ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ በመለኮቱ ፡ ከማርያም ፡ መወለድ ፡ አይችልምና ፡ ማር ያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ (THEOTOkOS) ልትባል ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ ክርክር ፡ ከአመጣ ፡ ቆይቶ ፡ ነበርና ፡ የዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በ፬፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኤፌሶን ፡ (ግሪክ) ፡ ከተማ ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ እንዲታይ ፡ ተወስኖ ፡ ነበር ። በዚሁም ፡ ጉባኤ

ንስጥሮስን ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ሆኖ ፡ ሊከራከር ፡ የቀረበው ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ቄርሎስ ፡ ነው ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ የሮማው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ሴሌስተ፡፩ኛ፡በሕብረትን፡በር።ስለዚህ፡በጉባኤው ፡ ላይ፡ብዙ ፡ ጥቅስ ፡ ከሐዲስና ፡ ከሌላውም ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ እየተጠቀሰ ፡ ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነቱና ፡ ሰውነቱ ፡ የተዋሃደ ፡ ፩ ፡ አካል ፩ ፡ ባሕርይ ፡ መሆኑን ፡ እመቤታችንም ፡ እመ ፡ አምላክ ፡ መባል ፡ እንደሚገባት ፡ ቄርሎስ ፡ ረቺ ፡ ንስጥሮስ ፡ ተረቺ ፡ ሆነው ፡ ተለያዩና ፡ ንስጥሮስ ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ሔደ ። የዚህ ፡ ክርክር ፡ በሃይማኖት ፡ አበው ፡ በ፸፫ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደዚሁም ፡ በራሱ ፡ በቄርሎስ ፡ መጽሐፍ ፡ (ነገረ ፡ ቄርሎስ) ፡ ከዚያም ፡ በቅዳሴ ፤ በመጽሐፈ ፡ ምሥጢር ፡ እያለፈ ፡ ይገኛል ። ስለራሱ ፡ መታሰቢያም ፡ በስንክሳር ፡ በሐምሌ ፡ ፫ ቀን ፡ የሚነበብለት ፡ ይገኛል ። ቄርሎስ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይን ፡ እየተከላከለ ፡ ኖሮ ፤ በ፬፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አውጣኪስ ፡ የሚባለው ፡ መነኵሴ ፡ ከ፬፻፵፫ ፡ ዓ፡ም፡ዠምሮ፡ከንስጥሮሳውያን ፡ ጋር ፡ እየተከላከለ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ እምነት ፡ አምኖ ፡ ሳለ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ከሰው ፡ የተለየ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አውጣኪስን ፡ በዚሁ ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ፍላቭያኖስ ፡ ረቂቅ ፡ ሥጋ ፡ እንዳይል ፡ በ፬፻፵፰ ዓ ፡ ም ፡ ከገዘተው ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይና ፡ የሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ጉዳይ ፡ እንደገና ፡ በቄርሎስ ፡ ተከታይ ፡ በዲዮስቆሮስና ፡ በፍላቭያኖስ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ መደበደብ ፡ እስኪጨመርበት ፡ ድረስ ፡ ትልቅ ፡ ክርክርና ፡ ጠብ ፡ ሆነ ። ይኸው ፡ ጉዳይ ፡ በዚሁ ፡ በዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ በጉባኤ ፡ ይታይ ፡ ተባለና ፡ በ፬፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኤፌሶን ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ ። በስብሰባው ፡ ላይ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ አሸነፈ ፡ ቭላቭያኖስ ፡ ተሸነፈ ፡ ተብሎ ፡ ተለያዩ ። ፍላብያኖስም ፡ በተሸነፈ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ሞተ ። የሞተውም ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ወገኖች ፡ (እንደሌሎቹም ፡ ራሱ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ጭምር) ፡ በደበደቡት ፡ ሕመም ፡ ነው ፡ ይባላል ። ከዚህ ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወገኖቹን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሹመቱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ በደስታ ፡ ተመለሰ ።

የዚህ ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር በጣም ፡ ተስፋፍቶ ፡ ግማሹ ፡ አርዮሳዊ ፤ ግማሹ ፡ ንስጥሮሳዊ ፡ ግማሹ ፡ አውጣቅሳዊ ፡ ግማሹ ፡ ያዕቆባዊ ፡ (የተዋህዶ ፡ ወገን) ፡ እየተባለ ፡ በጉባኤም ፡ ያለጉባኤም ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ በየመኳንንቱም ፡ ቤት ፡ በየገዳሙና ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ክርክሩ ፡ ሲቀልጥ ፡ ንጉሡ ፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ራሱ ፡ አውጣቅሳዊ ፡ (፩ ባሕርይ)፡ሆኖ ፡ ፩ አንድ ፡ ጊዜም፡ወደ፡ ፍላቭያኖስ ፡እያዘነበለ)፡ ሲከራከርና ፡ ሲያከራክር፡በመካከሉ፡ከሰሜን ፡ የሚያስፈራው ፡ ጠላት፡አቲላ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ የቁስጥንጥንያን ፡ መንግሥት ፡ ሊወረው ፡ ብቅ ፡ ማለቱ ፡ ተሰማ ። አቲላ ፡ የቅጽል ፡ ስሙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጅራፍ ፡ ነው ። የአቲላ ፡ ፈረስ ፡ ባለፈበት ፡ ምድር ፡ ሳር ፡ አይበቅልም ፡ ይባላል ። የአቲላና ፡ የአብዛኛ ፡ ሠራዊቱ ፡ የሁንስ ፡ መልካቸው ፡ ፋንጋ ፡ ቁመታቸው ፡ አጫጭር ፡ ምግባቸው ፡ እርጥብ ፡ ሥጋና ፡ ሥራሥር ፡ ነው ፡ ዘራቸው ፡ ሞንጐል ፡ ስለሆነ ፡ ከሞንጐል ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ዘረው ፡ ኤውሮፓ ፡ ከገቡ ፡

ቆይተዋል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የያዙት ፡ መደበኛ ፡ ምፍራቸው ፤ የዛሬው ፡ ሖንግሬ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ የአቲላ ፡ መምጣት ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ የሃይማኖቱ ፡ ጉዳይ ፡ ለጊዜው ፡ ከአሳብ ፡ ተወገደና ፡ ሁሉም ፡ ስለነፍሱ ፡ ድኅነት ፡ ወታደሩና ፡ ሹማምንቱ ፡ ስለው ጊያ ፡ ያስቡ ፡ ገ፫መር ። ንጉሡ፡ዳግማዊ፡ቴዎዶስዮስም፡ከነቤተ ፡ ሰቡ፡ከመኳንንቱ፡ጋር ፡ ሆኖ ፡ በበለጠ ፡ እየተጨነቀ ፡ ያስብ ፡ ጀመር ፡ በመጨረሻም ፡ ለመመለስ ፡ ኃይል ፡ የለንምና ፡ ብንገብር ይሻላል ፡ ብሎ ፡ ሊገብር ፡ ተላልኮ ፡ ቃረቀ ። ያም ፡ ሊያስገብር ፡ ዕርቁን ፡ ተቀብሎ ፡ ለጊዜው ፡ ወረራውን ፡ አቆመ ። ነገር ፡ ግን ፡ መኳንንትና ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ፈሪ ፡ በነቆስጠንጢኖስ ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ ይግዛ ፡ እያለ ፡ የሚያማውና ፡ የሚወቅሰው ፡ በረከተ ። በመጨረ ሻም ፡ በዚሁ ፡ ተናደው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል ። በዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ የተ ፈጸመውን ፡ የቁስጥንጥንያውንና ፡ የኤፌሶኑን ፡ ጉባኤ ፡ በትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የጻፉ ፡ አንዳንድ ፡ ያገራችን ፡ ሰዎች ፡ ተሳስተዋል ። ይኸም ፡ ስሕተት ፡ ሊደርስ ፡ የቻለው ፡ የጉባኤውን ፡ ዘመንና ፡ ሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ የነበ ሩበትን ፡ ጊዜ ፡ በለማገጣጠምና ፡ በለማመዛዘን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

መርቅያን ፡ (ማርቺያኑስ)፡ ፬፻፶-፬፻፶፯ ፡ ዓ፡ም ፡ – ኃይለኛው ፡<br>ወራሪ ፡ አቲላ–የዲዮስቆሮስ – መቃሠር ።

ቴዎዶስዮስ ፡ ዳግማዊ ፡ እንደሞተ ፡ እንደ ፡ ንግሥት ፡ አገሩን ፡ ታስተዳድር ፡ የነበረችው ፡ እኅቱ ፡ ፑልኼሪ ፡ (ብርክልያ፡) ነበረች ፡ እሷም ፡ በወታደርነት ፡ ስመ ጥር ፡ የሆነውን፡የጦር፡አለቃ ፡ መርቅያንን ፡ (ማርቺያኑስ) መርጣ ፡ አግብታ ፡ በወንድሟ ፡ ዙፋን ፡ አስቀመጠችው ። እሱም ፡ እዙፋኑ ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ አቲላ ፡ ግብሬን ፡ ላክ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡ መርቅያንም ፡ «የሚሰጥ ፡ ወርቅ ፡ ለወዳጄ ፤ ብረት ፡ ለጠላቴ ፡ አለኝ» ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። የዚህም ፡ ግልጽ ፡ ትርጓሜ ፡ በፍቅር ፡ ወዳጄ ፡ ለሆነ ፡ የምሰጠው ፡ ወርቅ ፡ አለኝ ፡ ላስገብርህ ፡ የሚለኝን ፡ ጠላቴን ፡ ደግሞ ፡ ተዋግቼ ፡ የምመልስበት ፡ ብረት ፡ አለኝ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ መልስ ፡ አቲላን ፡ አላስፈራ ውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአሳቡ ፡ ወደ ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ከመዝመት ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ብዘምት ፡ ይበልጥ ፡ ስም ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ቆረጠ ። ስለዚህ ፡ በየመንገዱ ፡ ያገኘውን ፡ እየዘረፈ ፡ እያፈረሰ ፤ እየተዋጋ ፡ እየማረከ ፡ እየገደለ ፡ እስከ ፡ ሮማ ፡ በራፍ ፡ ደረሰ ። ይህ ፡ ኃይለኛና ፡ ጨካኝ ፡ አስፈሪ ፡ ሰውዬ ፡ ሁሉን ፡ ለማድረግ፡ ሲጨክን ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖቻቸውን ፡ ለብሰው ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ ከተማችንን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ አታጥፋብን ፡ ብለው ፡ ሲለምኑት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይመለስ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። እንደዚሁም ፡ በፓሪስ ፡ (ያን ፡ ጊዜ ፡ ሉቲስ ) ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ሲጠጋ ፡ ሕዝቡ ፡ «አቲላ ፡ የት፡ደረሰ ፡ ይሆን ፡ ወዴት ፡ እን ቨሰ ፡ ይሆን እያለ ፡ በያለበት ፡ እየተርበደበደ ፡ ሲጨነቅ ፡ ቅድስት ፡ ዠኔቭዬቭ ፡ የም ትባለው ፡ መነኰሲት ፡ አይዟችሁ ፡ ምንም ፡ አያደርጋችሁም ፡ ብላ ፡ አረጋግጣ ፡ ስለ ነበርና ፡ በውነትም ፡ ሳያጠፋው ፡ ስለቀረ ፡ መነኰሲቷ ፡ እስከዛሬ ፡ በዚሁ ፡ ስሟ ፡ ሲነሣና ፡ ስትመሠገን ፡ ትኖራለች ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በቀረው ፡ አውራጃ ፡ በያለበት ፡ አቴላ ፡ የፈጸመው ፡ የጭ ካኔና ፡ የማፍረስ ፡ የማቃጠል ፡ ሥራ ፡ ጽኑ ፡ የሚሆኑትን ፡ መንግሥታት ፡ በንድ ፡ አኤቴውስ ፡ በሚባል ፡ ባንድ ፡ ሮማዊ ፡ ጄኔራል ፡ ውስጥ ፡ አብረው ፡ እንዲዋጉ ፡ አደረጋቸውና ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በካታሎኒክ ፡ (ፈረንሳዊ) ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ገጥመው ፡ ተዋጉት ። ቢሆንም ፡ እነሱም ፡ ሳያሸንፉት ፡ እሱም ፡ ሳያሸንፍ ፡ ከፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ወደኢጣልያ ፡ አገር ፡ መንደርና ፡ ከተማ ፡ እያቃጠለ ፡ ሽቅብ ፡ ወደሰሜን ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ እንደገባ ፡ በ፬፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተ ። ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ልጆቹ ፡ አልጋውን ፡ ለመውረስ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲዋጉ ፡ መንግሥታቸው ፡ ጠፋ ። የተ ረፈውም ፡ ሕዝብ ፡ ባንደኛው ፡ ልጁ ፡ እየተመራ ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ (ሺን) ፡ ገባ ።

አኤቴውስ ፡ ከአቲላ ፡ ጋር ፡ ባደረገው ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ እንደአሸናፊ ፡ ተቆ ጥሮ ፡ ዝናውና ፡ ክብሩ ፡ ስለገነነ ፡ በዚህ ፡ ቀንቶ ፡ የምዕራቡ ፡ የሮማ ፡ ግዛት ፡ ቄሣር ፡ ባሌንቲንያኖስ ፡ ራሱ ፡ በ፬፻፶፬ ፡ ገደለው ። የምሥራቁ ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ንጉሥ ፡ መር ቅያን ፡ ግን ፡ ገብርልኝ ፡ ብሎ ፡ አቴላ ፡ የላከበትና ፡ "የሚሸጥ ፡ ወርቅ ፡ ለወዳጄ ፡ ብረት ፡ ለጠላቴ ፡ አለኝ" ብሎ ፡ ከመለሰ ፡ በኋላ ፡ እንደዕድል ፡ አቴላ ፡ የእሱን ፡ ግዛት ፡ ትቶ ፡ ወደምዕራብ ፡ ከዞረለት ፡ ወዲህ ፡ እሱ ፡ ክብሩና ፡ ሥልጣኑ ፡ ሳይነካ ፡ ግዛቱን ፡ በሰላም ፡ ያስተዳድር ፡ ዠመር ። በዘመኑ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ወገን ተሸንፎ ፡ ተጠቃ ። በምዕራብ ፡ በሮማ ፡ በምሥራቅ ፡ በቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ ለክርስቶስ ፡ የሰውነትና ፡ የመለኮትነት ፡ ሁለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ የሚል ትምህርት ፡ ስለተስፋፋ ፡ በቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባዔ ፡ አሸንፎ ፡ ወደ እስክንድርያ ፡ የተመለሰው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ «የሰውነቱና ፡ የመለኮትነቱ ፡ ባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሆኗል» ፡ እያለ ፡ ስለአስተማረ ፡ በሁለቱ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ በረታ ። ስለዚህ ፡ በንጉሡ ፡ በመርቅያን ፡ በሚስቱ ፡ በብርክልያ ፡ ፈቃድ ፡ ነገሩ ፡ በጉባዔ ፡ እንዲታይ ፡ ተወሰነ ። ፮፻፴፮ ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ሊቃውንትም ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኬልቄዶን ፡ (ግሪክ) ፡ ተሰበሰቡ ። ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ተከታይና ፡ ደጋፊ ፡ ስለአላቸው ፡ ሳይሸናነፉ ፡ ስለቀሩ ፡ የሮማ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ ይመስክር ፡ ተብሎ ፡ ከሱ ፡ የተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ ቢነበብ ፡ „ሁለት ፡ ባሕርይን" ፡ የሚደግፍ ፡ ሆነ ። በዚያም ፡ ያሉት ፡ ጳጳሳት ፡ ሁለት ፡ ባሕርይን ፡ ተቀበል ፡ እምቢ ቃልህ ፡ ገዝተንሃል ፡ አሉት ፤ ዲዮስቆሮስም ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ በዚያ ፡ ያሉትን ፡ ጳጳሳት ፡ የሌለውን ፡ ልዮንን ፡ መልሶ ፡ ገዘታቸው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ በጉባኤው ፡ ታላቅ ፡ ሁከት ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በብርክልያ ፡ ትእዛዝ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተያዘና ፡ ጥርሱን እስኪሰበር ፡ ድረስ ፡ ደብድበው ፡ ጺሙን ፡ ነጭተው ፡ ወደ ፡ ጋንግራ ፡ ደሴት ፡ (ገላትያ–ትንሽ ፡ እስያ ፡) ወስደው ፡ እንዳሠሩት ፡ በ፬፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞተ ። እሱና ፡ የሹመት ፡ አባቶቹ ፡ እነአባ ፡ አትናቴዎስ ፡ እነአባ ፡ ቄርሎስ ፡ የተጋደሉበት ፡ ያንድ ባሕርይ ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፡ በእስክንድርያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በኑብያ ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ፡ በን ዳንድ ፡ አሳብ ፡ ከመለያየቱም ፡ በቀር ፡ በግሪክ ፡ በአርመን ፡ በመስኮብ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንም ፡ ጸድቋል ።

ዲዮስቆሮስ ፡ በሞተ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ በ፬፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጠላቱ ፡ ንጉሥ ፡ መርቃያን ፡ ያገሬችን ፡ መጽሐፍ ፡ „ንስጥሮሳዊ» ፡ የሚለው ፡ ሞተ ። ከሱ ፡ የበለጠ ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ደበኛ ፡ የነበረችው ፡ ብርክልያ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ከመሞቱ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ቀድማ ፡ በ፬፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሞታለች ።

<u>ልዮን ፡ ቄሣር ፡ (፬፻፵፯–፬፻፷፬ ፡ ዓ፡ ም ።)</u>

መርቅያን ፡ ሲሞት ፡ ልዮን ፡ የሚባለው ፡ ነገሠ ፡ በሱም ፡ ዘመን ፡ ዘሩ ፡ ከአርመኖች ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ አስፓር ፡ የሚባል ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ነበረው ፡ ይህም ፡ የጦር አለቃ ፡ በሥራውና ፡ በሥልጣኑ ፡ ንጉሡን ፡ እየተጫነ ፡ ሲኖር ፡ በመጨረሻም ፡ አስገደለው ። በልዮን ፡ ዘመን ፡ ቈስጥንጥንያ ፡ ተቃጠለች ።

<u>ዜኖን ፡ ቄሣር፡ (፬፻፷፬—፬፻፹፬ ፡ ዓ ፡ ም ።)</u>

ከልዮን ፡ በኋላ ፡ ዜኖን ፡ ነገሠ ፡ እሱም ። እንደነገሠ ፡ እነዚህ ፡ በየጊዜው ፡ አዳዲስ ፡ አሳብ ፡ እያፈለቁ ፡ የተለያዩት ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ይሁኑ ፡ “ሔኖቲኮን“ ፡ ሲል ፡ በ፬፻፸፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ አወጣ ። አሳቡ ፡ ክፉ ፡ አልነበረም ዳሩ ፡ ግን ፡ የማን ፡ አሳብ ፡ ወድቆ ፡ የማን ፡ አሳብ ፡ ሊጸና ፡ ? ስለዚህ ፡ አዋጁ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ሳያገኝ ፡ እንደዚሁ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ እንደተለያዩ ፡ ቀሩ ። እሱም ፡ ከምዕራብ ፡ ገዥዎች ፡ ከነ ፡ ክሎቢ ፡ (የፈረንሣዊ ፡ የመዠመሪያ ፡ ገዥዎች ፡ ) ጋር ፡ ሲከራከር ፡ እንደኖረ ፡ ሞተ ። በቈስጥንጥንያ ፡ መርቅያን ፡ (፬፻፵–፬፻፵፯) ፡ ልዮን ፡ (፬፻፵፯–፬፻፷፬) ፡ ዜኖን፡(፬፻፷፬–፬፻፹፬)፡አናስታስዮስ ፡ (፬፻፹፬–፭፻፲፫) ፡ በሚገዙበት፡ጊዜ ፡ ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ እነሶልአደባ ፡ እነአልዓሜዳ ፡ እነዋዚና ፡ (ዜና) ፡ የነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ አልዓሜዳ ፡ በነገሠ ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ፡ እነዚያ ፡ ስማቸውና ፡ ዝናቸው ፡ ባገራችን ፡ የታወቀው ፡ ዘጠኙ ፡ ቅዱሳን ፡ እነ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ለማስተማር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡ ።

<u>አናስታስዮስ ፡ ቄሣር ፡ (፬፻፹፬–፭፻፲፫) ዓ፡ ም፡</u>

ከዜኖን ፡ በኋላ ፡ አናስታስዮስ ፡ ነገሠ ። ታሪኩ ፡ በአስተዳደርና ፡ በሃማኖቱን ከክፉ ፡ ሥራ ፡ በማገድ ፡ ከዜኖንና ፡ ከልዮን ፡ ያበልጠዋል ። በዘመኑ ፡ በጨዋታና ፡ ሰውነትን ፡ በማጕልመስ ፡ እያመካኙ ፡ እቲያትሩ ፡ ቦታ ፡ በፈቃዱ ፥ ብዙ ፡ ሰው ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እየተማታ ፡ ይጋደል ፡ የነበረውን ፡ በሕግ ፡ ከለከለ ። በስሙ ፡ የሚጠራውን ፡ ቅጥርና ፡ ምሽግ ፡ ለጠላት ፡ መከላከያ ፡ አሠራ ። በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ እንደነ ፡ ዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይን ፡ (ሞኖፊዚት) ፡ ይደግፍ ፡ ነበር ።

## ዩስቲኖስ ፡ (፭፻፲፰–፭፻፳፯) ፡ ዓ ፡ ም ።

ከአናስታስዮታስ ፡ በኋላ ፡ ዩስቲኖስ ፡ ነገሠ ። እሱም ፡ ተራ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ስለ ነበረ ፡ ንባብና ፡ ጽሕፈት ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። የሃይማኖትንም ፡ ምሥጢ ርና ፡ ክርክር ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚሁ ፡ በመላ ፡ ወይም ፡ ለአ ስተዳደር ፡ እንዲመቻው ፡ ሁለት ፡ ባሕርዮን ፡ ደገፈ ። አርዮሳውያን ፡ እንዳያስተምሩ ፡ ከለከለ ። አንድ ፡ ባሕርይን ፡ ግን ፡ እንደዚሁ ፡ ተዋቸው ። በዩስቲኖስ ፡ ዘመነ ፡ መን ግሥት ፡ የተፈጸመውን ፡ አሳዛኝ ፡ የሀገረ ፡ ናግራን ፡ እልቂትንና ፡ ያሄ ፡ ካሌብን ፡ ተበቃይነት ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እንመለከታለን ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፫ ።

### ስለ ፡ ፱ኙ ፡ (ተሰዓቱ) ፡ ቅዱሳን ፡ ወደ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ።

አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ ከሞቱ ፡ ወዲህ ፡ ዝርዝሩ ፡ እንደሚያሳየን ፡ እስከ ፡ ካሌብ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ነገሥታት ፡ አልፈዋል ፡ በአብርሃና ፡ በካሌብ ፡ መካከል ፡ ፪፻ ፡ ዓመት ፡ የሚያህል ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ታሪክ ፡ በዘመኑ ፡ ተጽፎ ፡ ወደጊዜያችን ፡ ሳይተላለፍ ፡ በመቅረቱ ፡ ምን ፡ እንደተ ሠራ ፡ የሚታወቅ ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ የለም ።

በአልዓሚዳ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የ፱ኙ ፡ ቅዱሳን ፡ መምጣት ፡ ስለሚታወቅ ፡ አሁን ይኸንኑ ፡ እንጽፋለን ።

በቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ ከትልቁ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ወዲህ ፡ የክርስትና ፡ ሃይ ማኖት ፡ በጣም ፡ እየተስፋፋ ፡ መሔዱን ፡ ተመልክተናል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከትልቁ ፡ ቴዎዶስዮስና ፡ በተከታዮቹ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ ሊቃነ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፤ ቀሳውስት ፤ መነኮሳት ፡ በበረከቱ ፡ መጠን ፡ እርስ ፡ በር ሳቸው ፡ መለያየታቸው ፡ ያሳዝናል ። በችግሩና ፡ በስደቱ ፡ ዘመን ፡ በኔሮን ፡ በነዲ ዮቅልጥያኖስ ፡ ጊዜ ፡ የነበራቸው ፡ ኅብረትና ፡ አንድነት ፡ በአሁኑ ፡ በምቾቱ ፡ ጊዜ ፡ ጠፋና ፡ ባለፈው ፡ እንዳነበብነው ፡ የቁስጥንጥንያው ፡ ከእስክንድርያው ፡ የእስክንድር ያው ፡ ከሮማው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአሳብ ፡ እየተለያዩ ፡ ለክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ የለም ፡ ሁለት ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከወ ልድ ፡ ያንሳል ፡ የለም ፡ እኩል ፡ ነው ፤ ክርስቶስ ፡ በግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ዓረገ ፡ የለም ፡ በረቂቅ ፡ ነው ፤ እየተባባሉ ፡ በየጊዜው ፡ ፍጅትና ፡ ሁከት ፡ ሆነ ። ጳጳሳቱና ፡ ቀሳ ውስቱም ፡ የጊዜውን ፡ ንጉሥ ፡ ተደግፈው ፡ በሙግት ፡ ቀንቷቸው ፡ በተደላደሉ በት ፡ ሰዓት ፡ ደንበኛ ፡ ክርስትናን ፡ ብቻ ፡ ለሕዝብና ፡ ለአረማውያን ፡ በማስጠናት ፈንታ ፡ የያዙት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ የሁለት ፡ ባሕርይ ፡ እምነት ፡ ደኅና አድርጎ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እንዲመሠረት ፡ አብልጠው ፡ ይጥሩ ፡ ዠመር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚሁ ፡ በክርክሩና ፡ በሁከቱ ፡ መከከል ፡ ብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደ አፈ ፡ ወርቅ ፡ እንደቄርሎስ ፡ ከነዚያም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ . . .እንደ ፡ አርጌንስ፡ . . . ያሉት ፡ ከአእምሮአቸው ፡ ብዙ ፡ መንፈሳዊ ፡ አሳብና ፡ ዕውቀት ፡ አመነጩ ። ሁሉም ፡ በያለበት ድርጅቱን ፡ እያበጀ ፡ ክርስትናን ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ አደረገ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ ጳጳሳቱ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ምርመራና ፡ ርቀት ፡ በሔዱ ፡ መጠን ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ ልዩ ፡ አሳብ ፡ ሲያገኙና ፡ ያንን ፡ ማስተማር ፡ ሲጀምሩ ፡ ያንን ፡ የሚቃወመው ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ሲነሣ ፡ ተመልሶ ፡ ክርክር ፡ ይፈጠራል ። በክርክሩም ፡ ፩ኛው ፡ ወገን ፡ በተረታ ፡ ቁጥር ፡ መሪውን ፡ እስራት ተከታዩን ፡ ስደት ፡ ያገኙዋልና ፡ የተሰዓቱ ፡ ቅዱሳንም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ በዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ በ፬፻፴፩ ፡ ዓ ም፡ ንስጥሮስ ፡ ወደ ፡ አርዮስ ፡ እምነት ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይና ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ በሰጠና ፡ በዚሁ ፡ በእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በቄርሎስ ፡ በተረታና ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ቦታ ፡ በእሥራት ፡ ሲሄድ ፡ ወገኖቹ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ቻይና ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ተሰደዱ ።

፪ኛ ፡ በዚሁ ፡ በዳግማዊ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ጊዜ ፡ ፬፻፵፱ ፡ ዓ ም ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ለክርስቶስ ፡ መለኮታዊና ፡ ሰውነታዊ ፡ የሆኑ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተከራክሮ ፡ በረታው ፡ ጊዜ ፡ የፍላብያኖስ ፡ ወገኖች ፡ ተሰደዱ ።

፫ኛ ፡ ይኸው ፡ ራሱ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ለክርስቶስ ፡ መለኮቱና ፡ ሰውነቱ ፡ ተዋሕዶ ፡ ፩ ፡ ሆኗል ፡ ብሎ ፡ ፍላብያኖስን ፡ ከ፪ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የረታበት ፡ ነገር ፡ እንደገና ፡ ይኸን ፡ እምነት ፡ በማይደግፈው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በመርቅያን ፡ ቄሣር ፡ ጊዜ ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ም ፡ ተቀስቅሶ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ተደረገ ። በጉባኤውም ፡ ረቺና ፡ ተረቺ ፡ ስለጠፋ ፡ ምስክር ፡ በተቆጠረው ፡ በሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በልዮን ፡ ደብዳቤ ፡ ረቺ ፡ የነበረው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተመልሶ ፡ ተረቺ ፡ ሆኖ ፡ በንጉሡ ፡ በመርቅያንና ፡ በሚስቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ጢሙን ፡ ተነጭቶ ፡ ጥርሱን ፡ ተሰብሮ ፡ ሲታሠር ፡ እንደርሱ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ የሚሉት ፡ ወገኖች ፡ ከረቺዎቹ ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ መቀመጥ ፡ ጭንቅ ፡ ይሆንባቸዋልና ፡ በያለበት ፡ መሰደድ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። እነዚህ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ወገኖች ፡ (ሞኖፊስት) ፡ ለስደት ፡ የሚመርጡትም ፡ አገር ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ፩ባሕርይ ፡ የሚደግፈውን ፡ የክርስቲያኑን ፡ አገር ፡ ነው ። ሲጠፋ ፡ ደግሞ ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ የማይለው ፡ ያረመኔውም ፡ ወገን ፡ ማስጠጋቱ ፡ አይቀርም ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ወደ ፡ ዐረብ ፡ አገርና ፡ ወደምሥራቅ ፡ ብዙዎቹ ፡ ተሰደዋል ።

ስለዚህ ፡ የአክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከእብርሃ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ እምነቱን ፡ እንደያዘ ፡ ነው ። ለአንድ ፡ ባሕርይ ፡ እምነት ፡ ዋና ፡ መደብ ፡ ከሆነው ፡ ከእስክንድርያ ፡ እየተሾመ ፡ አክ

ሱም ፡ መጥተው ፡ ከአክሱም ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ የሚቀመጡት ፡ ጳጳሳትም ፡ ቀድሞም ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ ቄርሎስን ፡ አሁንም ፡ ተረታህ ፡ ተብሎ፡የታሠረውን ፡ ዲዮ ስቆሮስን ፡ ከልብ ፡ አምነው ፡ የሚከተሉት ፡ መሆናቸው ፡ በቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ የታወቀ ፡ ሆኗል ። በአክሱም ፡ ከግብፅ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ከአንጾኪያ ፡ ከሶርያ ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ለሥጋዊም ፡ ለመ ንፈሳዊም ፡ ጉዳይ ፡ ሲመላለሱ ፡ እንደዚሁም ፡ ከአክሱምና ፡ ከየአውራጃው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመላለሱ ፡ ነበር ።

በኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ እንደምናገኘው ፡ በ፫፻፹፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ ፓውሊን ፡ (ጳውሎሊት) ፡ የምትባል ፡ ሮማዊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ገድማ ፡ የምትኖር ፡ ለጓደኛዋ ፡ ሮማ ፡ ላለች ፡ ማርሴሊን ፡ ለምትባል ፡ ስት ጽፍ ፡ እንደዚህ ፡ ብላለች ፡ «እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ፡ ስለአርመኖች ፡ ስለ ፡ ሕንዶች ፡ ስለኢትዮጵያውያን ፡ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ቦታ ፡ ለመምጣት ፡ የሚሽቀዳደሙ ፡ ትሩፋት ፡ ለማድረግም ፡ የሚሻሙ» ።

በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ተሰዓቱ ፡ ቅዱሳን ፡ የሚባሉት ፡ ያንድ ባሕርይ ፡ ተከታዮች ፡ ከሆኑት ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ተከታዮች ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ከሁለት ፡ ባሕርዮች ፡ ለመሸሽ ፤ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ክርስትናን ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ መንገድ ፡ በወገናቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ለማስፋ ፋት ፡ በአልዓሜዳ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (፬፻፹-፬፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ) ወደ ፡ አክሱም ፡ መጡ ። ስማቸውና ፡ የመጡበት ፡ አገር ፡ ገድላቸው ፡ እንደሚለው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ዓይነት ፡ ነው ።

| ተርታ ፡ | ስም ፡ | የመጡበት ፡ አገር ። |
|---|---|---|
| ፩ኛ ፡ | ዘሚካኤል ፡ (አረጋዊ) ፡ | ሮም ፡ |
| ፪ኛ ፡ | ጳንጠሌዎን ፡ | » |
| ፫ኛ ፡ | ገሪማ ፡ (ይስሐቅ ፡) | » |
| ፬ኛ ፡ | ሊቃኖስ ፡ | ቁስጥንጥንያ ። |
| ፭ኛ ፡ | ይምዓታ ፡ | ቆስያ ፡ (መንፌ—ሲሲል) ፡ ኢጣሊያ ። |
| ፮ኛ ፡ | ጽሕማ ፡ | አንጾኪያ ፡ (ሶርያ) ፡ |
| ፯ኛ ፡ | ጉባ ፡ | ኪልቅያ ፡ (ግሪክ) ፡ |
| ፰ኛ ፡ | አፍጼ ፡ | እስያ ፡ |
| ፱ኛ ፡ | አሌፍ ፡ | ቂሣርያ ፡ |

የ፫ቱን ፡ የመዠመሪያዎቹን ፡ ሮም ፡ ብሎ ፡ የሊቃኖስን ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ሲል ፡ ሮም ፡ የሚባለው ፡ ያው ፡ ቁስጥንጥንያ ፡ ስለሆነ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ሊሆን ፡ አይ ችልም ፡ ወይም ፡ ሮም ፡ ያለው ፡ የቁስጥንጥንያን ፡ ግዛት ፡ ሳይሆን ፡ የኢጣል ያኑን ፡ ከተማና ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መደብ ፡ የሆነችውን ፡ ሮማን ፡ እንደሆነ በትክክል ፡ አይታወቅም ። አሌፍ ፡ የመጣበት ፡ ቂሣርያም ፡ እንደዚሁ ፡

ሁለት ፡ አገር ስለሆነ ፡ ያደናግራል ። ቂሣርያ ፡ የሚባል ፡ ከተማ ፡ በቀጳዶቅያ ፡ አጠገብ ፡ በዛሬው ፡ የቱርክ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ፪ኛው ፡ ደግሞ ፡ በፓለስቲን ፡ ሰሜን ፡ ሄሮድስ ፡ አውግስጦስ ፡ ቄሣርን ፡ ለማስደሰት ፡ ሲል ፡ በርሱ ፡ የሠየማት ፡ እሜዲቴራኔ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ የምትገኝ ፡ የፊልጶስ ፡ ቂሣርያ የምትባል ፡ አለች ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ የመጡበት ፡ ክፍል ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ ከሶርያ ፡ ስለሆነ ፡ ለሶርያ ፡ የሚቀርበው ፡ የመዠመሪያው ፡ ነውና ፡ አሌፍ ፡ የመጣው ፡ ከዚያ ፡ በመሆኑ ፡ አሳባችንን ፡ በዚሁ ፡ እናቁምና ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ጉዳይ ፡ እንተላለፍ ።

እነዚህ ፡ ፱ኙ ፡ ቅዱሳን ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የመሠረተውን ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ በተለይ ፡ በ፩ ፡ ባሕርይና ፡ በተዋሕዶ ፡ መንገድ ፡ በያውራጃው ፡ ተበትነው ፡ በዓትና ፡ ገዳም ፡ እያበጁ ፡ አስፋፉ ። በዚህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ታቦት ፡ በስማቸው ፡ እያስቀረጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እያሠራ ፡ ብፁዓን ፡ ቅዱሳን ፡ አድርጎ ፡ ያከብራቸዋል ። ከነዚህ ፡ መካከል ፡ ደግሞ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎቹና ፡ ደምቀው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የታወቁት ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ የተባሉት ፡ ዘሚካኤል ፡ ናቸው ። እርሳቸውም ፡ በትልቁ ፡ ተራራ ፡ ገዳም ፡ በደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገድመው ፡ ገዳሙን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እየሄደ ፡ እስከዛሬ ፡ ይሳለመዋል ። እንደዚሁም ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፤ አባ ፡ ገሪማ ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የክርስቲያን ፡ ወገንና ፡ ይልቁንም ፡ ገዳማቸው ፡ በሚገኝበት ፡ በትግሬ ፡ አገር ፡ የከበሩ ፡ ናቸው ።

ከነዚህ ፡ ከ፱ኙ ፡ መካከል ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ አባ ፡ ገሪማ ፡ አባ ፡ እፍጼ ፡ ገድልና ፡ ድርሳናቸው ፡ በየገዳማቸው ፡ ይገኛል ፡ ከዚያም ፡ ወደፈረንጅ ፡ አገር ፡ የብራናው ፡ ጽሑፍ ፡ ተሻግሮ ፡ በፓሪስ ፡ በሎንዶን ፡ በሮማ ፡ ይገኛል ። ከዚያም ፡ የአባ ፡ ገሪማንና ፡ የአባ ፡ ጰንጠሌዎንን ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የአቡነ ፡ አረጋዊን ፡ ኢኛሲዮ ፡ ጉይዲ ፡ አሳትመውታል ።

የአቡነ ፡ አረጋዊንም ፡ የአቡነ ፡ ገሪማንም ፡ ገድል ፡ የጻፉት ፡ የአክሱም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ናቸው ። የአባ ፡ ገሪማን ፡ ገድል ፡ የጻፈው ፡ በገድሉ ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ እንደሚታየው ፡ "ድርሳን ፡ ዘደረሰ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ዘአክሱም ፡ በእንተ ፡ እበዩ ፡ ወክብሩ ፡ ለቅዱስ ፡ ይስሐቅ ፡ (ገሪማ) . . . . ,, ብሎ ፡ ይዠምራል ፡ ከዚያ ፡ "ወሀሎ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ መስፍያኖስ ፡ ንጉሠ ፡ ሮም ፡ ወስመ ፡ ብእሲቱ ፡ ስፍንግያ ፡ እስመ ፡ መካን ፡ ይእቲ ፡ ወአልባ ፡ ውሉደ ፡ ወነበሩ ፡ ክልኤሆሙ ፡ እንዘ ፡ የኀዝኑ ፡ ፲ወ፱ተ ፡ ዓመተ ፡ . . . . ,, እያለ ፡ ይቀጥልና ፡ በጭሩ ፡

ሀ- ገሪማ ፡ ከሮም ፡ ንጉሥ ፡ መወለዱንና ፡ ስሙ ፡ ይስሐቅ ፡ ትርጓሜው ፡ ዕንቁ ፡ ባሕርይ ፡ ተብሎ ፡ መሠየሙን ።

ለ- ተወልዶ ፡ መንፈሳዊ ፡ መጻሕፍትን ፡ እየተማረ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ ሚስት ፡ እንጭለትና ፡ በሠርጉ ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ እያሉ ፡ ሲመከከሩ ፡ "ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ተገልጾ ፡ ብዙ ፡ ነፍስ ፡ የሚያድነው ፡ መኖሩን ፡ በስሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠራቱንም ፡ ገልጾ ፡ መናገሩን ።

ሐ· አባቱ ፡ መስፍያኖስ ፡ ሲሞት ፡ መኳንንቱ ፡ እምቢ ፡ እያለ ፡ ሲያለቅስ፡ በግድ ፡ አንግሠውት ፡ ሳለ ፡ በአባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ አሳሳቢነት ፡ በቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ መሪነት ፡ ከሮም ፡ ተነሥቶ ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ አክሱም ፡ ደርሶ ፡ ከአባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ መገናኘቱንና ፡ ምንኵስናን ፡ አስኬማን ፡ ከርሳቸው ፡ መቀበሉን ፤ የአባ ፡ ገሪማን ፡ (ይስሐቅን) ወደ ፡ አክሱም ፡ መምጣት ፡ ሲሰሙ ፡ የቀሩት ፡ አባ ፡ ሊቃኖስ ፡ ከቊስ ጥንጥንያ ፡ አባ ፡ ይምዓታ ፡ ከቆስያ ፡ የቀሩትም ፡ ከየሥፍራቸው ፡ ወደ ፡ አክሱም፡ መምጣታቸውን ።

መ· ሁሉም ፡ አክሱም ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ የአክሱም ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ወደነርሱ ፡ መጥቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚገዛት ፡ ሰውም ፡ መኳንንቱም ፡ ሕፃን ፡ ልጃ ፡ ገረድ ፡ ግብር ፡ በየቀኑ ፡ እየገበሩ ፡ የሚገዙለት ፡ ዘንዶ ፡ (አርዌ) አለ ፡ ብሎ ፡ እንደነገራቸ ውና ፡ በዚሁ ፡ ተገርመው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልየው ፡ በጸሎታቸው ፡ አር ዌውን ፡ እንደገደሉት ።

ሠ· ይስሐቅ ፡ በዓቱን ፡ በመደራ ፡(መጠራ ?)፡ አድርጎ ፡ በየጊዜው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሚ ያስደንቅ ፡ ተአምራት ፡ ማድረጉን ፡ ፀሐይ ፡ ማቆሙን ፡ ዛፎችና ፡ ደንጋዮችም ፡ እየታ ዘዙት ፡ ብዙ ፡ የጽድቅና ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ በሰኔ ፡ ፲፯ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተሠውሮ ፡ ወደሰማይ ፡ መውጣቱን ፡ ይገልጻል ።

የቁሩትንም ፡ ቅዱሳን ፡ የአባ ፡ አረጋዊንም ፡ የአባ ፡ ጰንጠሌዎንንም ፡ ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ብናነብ ፡ የምናገኘው ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉን ፡ ለመጨመር ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ ፡ ያንሰናል ። በገድሉም ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ አምኖ ፡ ለመቀበል ፡ ብዙ ፡ የሚቸግር ፡ ነገር ፡ አለ ። በዚሁ ፡ በገሪማ ፡ ገድል ፡ ወይም ፡ ድርሳን ፡ ላይ ፡ ገሪማን ፡ (ይስሐቅን) መስፍያኖስ ፡ የሚ ባለው ፡ የሮማ ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ያደርገዋል ። መስፍያኖስ ፡ የሚለውም ፡ መክስ ምያኖስን ፡ ይመስላል ። ይኸውም ፡ ቄሣር ፡ የዲዮቅልጥያኖስ ፡ ጓደኛ ፡ የነበረ ፡ በአረማዊነቱ ፡ የጸና ፡ የክርስቲያን ፡ ጠላት ፡ ነው ። የነበረበትም ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ ሳይገባ ፡ በ፫፻፰-፫፻፲፫ ዓ. ም. መካከል ፡ ነው ። ከርሱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ መክስምያኖስ ፡ ወይም ፡ መስፍያኖስ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ የለም ። ልጁም ፡ መንግሥቱንና ፡ ዙፋኑን ፡ ንቆ ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ሄደ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ በሮማውያን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በፍጹም ፡ ስለሌለ ፡ ነገሩን ፡ መቀ በል ፡ ይቸግራል ።

ስለዚህ ፡ ስለተሰዓቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ልናምን ፡ የሚገባው ፡ በመዠመሪያው ፡ ምዕ ራፍ ፡ እንደተተረከው ፡ እነዚህ ፡ ቅዱሳን ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ከሶርያ ፡ መጥተው ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የመሠረተውን ፡ ክርስትና ፡ በበለጠ ፡ ማስፋፋታ ቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው። በዚሁም ፡ ሥራቸው ፡ በቤተ ፡ መንግሥትም ፡ በቤተ ፡ ክህነትም ፡ ተከብረው ፡ ጽላት ፡ ቢቀረጽላቸው ፤ ለመታሰቢያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢሠራላቸው፤ የበዓል ፡ ቀን ፡ ቢወሰንላቸው ፡ የተገባ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በየገድላቸውና ፡ በስንክሳር ፡ እንደተመለከተው ፤

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የአባ ፡ | አሌፍ ፡ | በዓል ፡ | በመጋቢት ፡ | ፲፩ ፡ ቀን ፡ |
| ,, | ጽሕማ ፡ | ,, | በጥር ፡ | ፲፯ ፡ ,, |
| ,, | አረጋዊ ፡ | ,, | በጥቅምት ፡ | ፲፬ ፡ ,, |
| ,, | አፍጼ ፡ | ,, | በግንቦት ፡ | ፲፪ ፡ ,, |
| ,, | ገሪማ ፡ | ,, | በሰኔ ፡ | ፲፯ ፡ ,, |
| ,, | ጳንጠሌዎን ፡ | ,, | በጥቅምት ፡ | ፯ ,, |
| ,, | ሊቃኖስ ፡ | ,, | በኅዳር ፡ | ፳፯ ,, |
| ,, | ጉባ ፡ | ,, | በግንቦት ፡ | ፳፱ ,, |
| ,, | ይምዓታ ፡ | ,, | በጥቅምት ፡ | ፳፫ ,, |

ሲከበር ፡ ይኖራል ።

የመጡበትን ፡ ዘመን ፡ አንዳንዱ ፡ በካሌብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ግማሹም ፡ በልጁ በገብረ፡መስቀል ፡ ጊዜ ፡ የሚያደርገው ፡ አለ። ነገር፡ ግን ፡ ደንበኛው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ «ወሳልዓዶባ ፡ ወለዶ ፡ ለአልዓሜዳ ፡ ዘወጽኡ ፡ በመዋዕለ ፡ መንግሥቱ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ እምድረ ፡ ሮም ፡ (ይኸውም ፡ ማለት ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡) ወእስ ተራትኡ ፡ ሃይማኖተ ፡ ወሥርዓተ ፡ ምንኵስና ፡ . . . » የሚለው ፡ ከብዙ ፡ ባለታሪክ ፡ ጋር ፡ ስለሚጋጠም ፡ ያመጣጣቸውን ፡ ጊዜ ፡ እዚሁ ፡ አልዓሜዳ ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ (፬፻፸–፬፻፹ ፡ ዓ፡ ምሕረት ፡) መመደብ ፡ የተስማማ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደፊት ፡ እንደምናገኘው ፣ ከነዚሁ ፡ ከተሰዓቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ አባ ፡ ጳንጠሌዎን ፡ ከአጼ ፡ ካሌብ ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ ከአጼ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ክርስትና ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ገዳምና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንፃ ፡ በመ ንፈሳዊ ፡ በኵል ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ሆነው በሕብረትና ፡ በጠበቀ ፡ ግንኙነት ፡ አብረው ፡ እየሠሩ ፡ ጊዜያቸውን ፡ አሳልፈዋል ።

እነዚህም ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ገዳማትን ገድመዋል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ፡ | አባ ፡ | አረጋዊ ፡ | ደብረ ፡ ደሞን ። |
| ፪ኛ ፡ | ,, | አሌፍ | የብኅዛን ፡ (አህስአ) ገዳም ። |
| ፫ኛ ፡ | ,, | ጽሕማ ፡ | የጼድያን ፡ ,, |
| ፬ኛ ፡ | ,, | አፍጼ ፡ | የዩሃን ፡ (ያሓ ፡) ,, |
| ፭ኛ ፡ | ,, | ገሪማ ፡ | የመደራን ,, |
| ፮ኛ ፡ | ,, | ጳንጠሌዎን ፡ | አክሱም ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ። |
| ፯ኛ ፡ | ,, | ሊቃኖስ ፡ | የደብረ ፡ ቆናጽልን ። |
| ፰ኛ ፡ | ,, | አባ ጉባና ፡ አባ ፡ ይምዓታ ፡ | በገርዓልታ ። |

በነዚህ ፡ በስማቸው ፡ የሚጠሩትን ፡ ገዳማት ፡ ዝርዝሩን ፡ በትክክል ፡ በና ውቀውም ፡ ቅዱሳኑ ፡ በዓታቸው ፡ ሆኖ ፡ ሲያስተምሩበት ፡ በነበሩበትና ፡ በሞቱ በት ፡ ሥፍራ ፡ በየጊዜው ፡ ገዳማቱንና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቱን ፡ የሚያሠሩት ፡ በሕዝብና ፡ በአገረ ፡ ገዥዎች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ነገሥታቱ ፡ እንደ ሚሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፶፩ ።

## የአክሱምና ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥታት ፡ የሥልጣኔ ፤ የፖለቲክ ፡ አንድነትና ፡ ግ ን ኙ ነ ት ።

በዚህ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ በአክሱም ፡ የገናንነት ፡ ዘመን ፡ አኲያ ፡ ገናና ፡ ሥልጡን ፡ ክርስቲያን ፡ የሆነውን ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ ነገሥታት ፡ አጫጭር ፡ ታሪክ ፤ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ በግብፅ ፡ የገነነውን ፡ የነአሞንን ፡ የነፕታህን ፤ የነስራፒስን ፤ በግሪክና ፡ በሮማ ፡ ግዛት ፡ የነበሩትን ፡ የነጁፖቬን ፤ የነማርስን ፡ አምልኮ ፡ የክርስቶስ ፡ ሐዋርያት ፡ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የተከተሉት ፡ ሰማዕታትና ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት በነቆስጠንጢኖስ ፡ በነቴዎዶስዮስ ፡ ዘመን ፡ እንደምን ፡ እንደደመሰሱት ፡ ተመልክተናል ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ሊቃን ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ መነኮሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ በመከከላቸው ፡ ራሳቸው ፡ በምርምር ፡ እየተፈላለጉ ፡ በሚያፈልቁት ፡ አሳብ ፡ እንደምን ፡ እንደተከራከሩ ፡ ተገንዝበናል ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የኛ ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፡ ያልን እንደሆን ፡ ለዚህ ፡ የነገሥታቱ ዜና ፡ መዋዕል ፡ እንደቍስጥንጥንያ ፡ ነገሥታት ፡ በየዘመኑ ፡ በየመልኩ ፡ ተጽፎ ፡ አልተገኘም ። የአስተዳደሩ ፡ የሕጉ ፡ የዳኝነቱ ፡ የገንዘቡ ፡ የገቢያው ፡ የሕንፃው ፡ የጦር ፡ መሣሪያው ፡ የቤት ፡ ዕቃው ፡ ዓይነቱና ፡ ሠሪው ፡ ሁሉ ፡ የተዘረዘረበት ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ በዘመኑ ፡ ጽፎ ፡ ያስተላለፈው ፡ አለመኖሩን ፡ አመልክተናል ። የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ እያለው ፡ እንደሌለው ፡ ሊመስል ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ከ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ምሥጋና ፡ የሚገባቸው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ አገራችን ፡ እየመጡ ፡ ከቆመው ፡ ተሰብሮ ፡ ከተጋደመው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ ፍራሽ ፡ ከነበረበት ፡ እየተፈላለጉ ፡ በዘመኑ ፡ የተቀረጸውን ፡ የብረት ፡ የናስ ፡ የብር ፡ የወርቅ ፡ ገንዘብ ፡ እየለቀሙ ፡ ጽሑፉን ፡ ተርጕመው ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ሲያወጡት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፤ ፫ ፡ ወይም ፡ ፬ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እስላሞች ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ የነበረው ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ታላቅ ፡ ድርጅት ፡ ያለው ፡ ደንበኛና ፡ ሥልጡን ፡ መንግሥት ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ቻሉ ። ባለፈው ፡ እንዳነበብነው ፡ የዒዛና ፡ ገናናነትንና ፡ ኃይል ፡ የሚገልጸው ፡ የሐውልት ፡ ጽሑፍ ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ የቀሩትንም ፡ ያልተጻፈላቸውን ፡ ይገልጻል ፡ ማለት ፡ እንችላለን ።

ከዒዛና ፡ በፊትና ፡ በኋላም ፡ ያሉት ፡ በአስተዳደር ፡ ግዛት ፡ በማስፋፋት ፡ ያው ፡ እንደርሱ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ መጥተው ፡ በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተስፋፍተው ፡ ስማቸው ፡ ሳባውያን ፡ ሀበሳን ፡ አግዓዝያን ፤ የሚባሉት ፡ ዘሮች ፡ ዘራቸውን ፡ ቋንቋቸውን ፡ ሥልጣኔያቸውን ፡ በምጥዋ ፤ በዳህላቅ ፤ በባርካ ፡ በሳሆ ፤ በማርያ ፤ በቤት ፡ አጽገባ ፤ በአድ ፡ ተክሌ ፤ በወዲህኛውም ፡ ትግሬ

በሐማሴንና ፤ በአከለ ፡ ጉዛይ ፡ በሠራዬ ፡ እስከ ፡ ዋጀራትና ፡ አሸንጌ ፡ ድረስ ፡ ከአስፋፋ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ለግዛትና ፡ ለአስተዳደር ፡ ወይም ፡ በምሪትና ፡ በመሰማራት ፡ እያለፉ ፡ ወደ ፡ አማራው ፡ አገር ፡ ወደበጌምድርና ፡ ወደ ፡ ጐጃም ፡ ወደሸዋ ፡ እየዘለቁ ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ዛሬ ፡ ልማዱና ፡ ቋንቋው ፡ የሰዉ ፡ መልኩ ፡ ሳይቀር ፡ እንደሚያስረዳን ፡ እስከ ፡ ጉራጌ ፡ እስከ ፡ ጋፋት ፡ ከወዲህም ፡ እስከ ፡ አርጎባ ፡ (አንከበር ፡ ምሥራቅ) ፡ እስከ ፡ ሐረር ፡ ደረሱ ። በነዚህም ፡ አገሮች ፡ ዘራቸውንና ፡ ቋንቋቸውን ፡ ልማዳቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ሲመሠረቱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አብሯቸው ፡ ካለው ፡ ከነዋሪው ፡ ከኩሽ ፡ ዘር ፡ ከበጅያው ፡ ከአገው ፡ ከሲዳማው ፡ ከጋላው ፡ ከሻንቅላው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ዘራቸውንም ፡ ልማዳቸውንም ፡ ደባልቀው ፡ ይገኛሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ መናገሻ ፡ ከተማውን ፡ አክሱም ፡ ያደረገው ፡ መንግሥት ፡ ሁሉንም ፡ በበላይ ፡ ያስተዳድር ፡ ነበር ። አክሱም ፡ በአራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ ክርስትናን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ ሃይማኖት ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ከሚመጡት ፡ መነኮሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ጋር ፡ በየግዛቱ ፡ ያስፋፋ ፡ ዠመር ። የቤቱ ፡ ሕንፃ ፡ የየሐውልቱ ፡ ቅርጽ ፡ የቀድሞው ፡ የፊለቁበትን ፡ የአሶርንና ፡ የባቢሎንን ፡ ምልክት ፡ ይዞ ፡ የደቡብ ፡ ዐረብን ፡ ከወዲህ ፡ የግብፅን ፡ እየነካ ፡ በጠቅላላው ፡ የግሪክን ፡ የሚመሳስል ፡ ይሆኑ ፡ ዠመር ። በምዕራፉ ፡ ላይ ፡ ጽሑፉን ፡ ከነስእሉ ፡ የተመለከትነው ፡ የነገሥታቶቻችን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የወርቅና ፡ የናሐስ ፡ ገንዘብ ፡ የቅርጹ ፡ ዓይነትና ፡ መጠን ፡ የነጋሢው ፡ መልክ ፡ የዙሪያው ፡ ሐረግና ፡ የጽሑፉ ፡ ቃል ፡ ከጎደኞቻቸውና ፡ በአንድ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ ከነበሩት ከሮማና ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ነገሥታት ፡ ከነዲዮቅልጥያኖስ ፡ ከነቴዎዶስዮስ ፡ ገንዘብ ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ተመሳሳይነት ፡ አለው ። አንዳንዱም ፡ ወደፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ይጠጋል ።

በኡብርሃ ፡ (ዒዛና) ፡ ሐውልቶች ፡ ላይ ፡ ያየነው ፡ «ዒዛና ፡ ወልደ ፡ እለ ፡ ዓሜዳ ንጉሠ ፡ አክሱም ፡ ወዘሕሜር ፡ ወዘረይዳን ፡ ወዘሰብእ ፡ ወዘሰልሄን» ፡ እያለ ፡ የእገሌ ፡ ልጅ ፡ የእገሌና ፡ የእገሌ ፡ አገሮች ፡ ንጉሥ ፡ እያሉ ፡ ጽሑፍን ፡ መዠመር ፡ የፋርሶችም ፡ የምሥራቃውያንና ፡ የአውሮፓውያንም ፡ ነገሥታት ፡ ልማድ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ይለናል ። የዚህንም ፡ ዓይነት ፡ አጻጻፍ ፡ ከአክሱምና ፡ ከዛጕዬ ፡ ተቀብለው ፡ በሸዋም ፡ በጐንደርም ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታቶቻችን ፡ በዘመኑ ፡ የሚገዙትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ እየጠቀሱ ፡ እንደተጠሩበት ፡ ወደፊት ፡ እናነባለን ።

በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከገቡት ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ከሌሎቹ ፡ የቁስጥንጥንያው ፡ ይበረክት ፡ ይመስለኛል ። ለምሳሌ ፡ ከቁስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ እየመጡ ፡ ያስተማሩት ፡ ይሁን ወይም ፡ ከዚህ ፡ የኛዎቹ ፡ ሊቃውንትና ፡ ቀሳውስት ፡ ወደነኛ ፡ ሄደው ፡ እየተማሩ ፡ ተመልሰው ፡ ባገራቸው ፡ ያገቡት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ይሁን ፡ በአክሱሞች ፡ ዘመን ፡ በዛጕዬዎች ፡ ጊዜ ፡ በየገዳማቱ ፡ በየአድባራቱ ፡ ውስጣዊ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ተስሎ ፡ የሚታየው ፡ የእመቤታችን ፡ ከልጅዋ ፡ ጋር ፡ (ምስለ ፡ ፍቁር ፡ ወልዳ) ፡ የመላእክትና ፡ የሰማዕታት ፡

ስዕል ፡ በቁስጥንጥንያ ግዛት ፡ በንቅድስት ፡ ሶፍያ ፡ ወይም ፡ ከ፩፻ ፡ እስከ ፡ ሺ፰፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ከተሳሉት ፡ ስዕሎች ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይነቱ ፡ ትክክል ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ የአክሱምና ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ መንግሥታት ፡ በንድ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ እንደመኖራቸው ፡ መጠን ፡ ሃይማኖትና ፡ ዕውቀት ፡ ተካፋይ ፡ ተፎካካሪና ፡ ወዳጅ ፡ መሆናቸውን ፡ እንረዳለን ። በፍሬምናጦስ ፡ የጵጵስና ፡ ሹመት ፡ ምክንያት ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቁንስጣ ፡ (ኮንስታንሲዩስ) ፡ ለአብርሃና ፡ ለአጽብሐ ፡ በጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ «የተከበራችሁ ፡ ወንድሞቼ» ፡ በሚል ቃል ፡ ደብዳቤውን ፡ ሲዘጋው ፡ ይበልጥ ፡ አሳባችንን ፡ ያጸናዋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ የናግራንን ፡ ክርስቲያኖች ፡ አይሁዶችና ፡ አረማውያን ፡ ተባብረው ፡ ሲያጠቁዋቸው ፡ የአክሱምና ፡ የቁስጥንጥንያ ፡ ነገሥታት ፡ ተባብረው ፡ ሲያድኑዋቸው ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ በሰፊው ፡ እንመልከት ።


## ምዕራፍ ፡ ፱፰ ።

**በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ግዛት—በደቡብ ፡ ዓረብ ፡ የክርስቲያኖችና ፡ የአይሁዶች ፡ ፉክክር—የሀገረ ፡ ናግራን ፡ ክርስቲያኖች ፡ እልቂት ።**

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ካሌብ ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ዘምቶ ፡ የናግራን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ደም ፡ የተበቀለበትን ፡ ታሪክ ፡ ከመመልከታችን ፡ በፊት ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ቀዳሚና ፡ ተያያዥ ፡ የሆነውን ፡ አሳብ ፡ እንገንዘብ ። ከስመ ፡ ጥሩው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከካሌብ ፡ በፊት ፡ ከአብርሃ ፡ ወዲህ ፡ ያሉት ፡ የአክሱም ፡ ነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ ታሪካቸው ፡ በማይገኝበት ፡ መካከል ፡ የካሌብ ፡ በናግራን ፡ ዕልቂት ፡ ምክንያት ፡ ሲገኝ ፡ ስለርሱ ፡ እስከ ፡ ተቻለ ፡ ድረስ ፡ በርከት ፡ አድርገን ፡ ለመጻፍ ፡ ለታሪካችን ፡ ያለን መጓጓት ፡ እያስገደደ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ከአክሱም ፡ መንግሥት ፡ አቀጣጫ ፡ ከኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ማዶ ፡ ከሚገኘው ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ምናልባት ፡ ከሺ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ ሳባ ፡ ሂሚያሪት ፡ አግዓዝያን ፡ ሀበሳን ፡ እያልን ፡ እኛም ፡ ጸሐፊዎቹም ፡ እየደጋገምን ፡ የምንጠራቸው ፡ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ መሻገራቸውን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተናግረናል ።

ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ በመጡበት ፡ በአፍሪካ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ ተመሥርተው ፡ ያገር ፡ ተወላጁን ፡ የካምና ፡ የኰሽን ፡ ዘር ፡ አሸንፈው ፡ ገዥውም ፡ አሠልጣኙም ፡ ሲሆኑ ፡ እያደርም ፡ ድርጅታቸው ፡ ሲበረታ ፡ ገናንነት ፡ ሲሰማቸው ፡ ፊታቸውን ፡ ወደመጡበት ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ አገር ፡ መለሱና ፡ የደቡብን ፡ አገር ፡ በዚያ ፡ ያሉትን ፡ የየነገዱን ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ ባላባት ፡ አሸንፈው ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ተገዥ ፡ አደረጉትና ፡ እንደራሴዎቻቸውን ፡ በዚያ ፡ እየሾሙ ፡ ያስተዳድሩ ፡ ጀመር ።



ተ·፯ መ·

ኢትዮጵያን ፡ ከግብፅ ፡ ከአሶርና ፡ ከባቢሎን ፡ ከደቡብ ፡ አረብ ፡ መንግሥታት ፡ ጋር ፡ የሚያሳይ ፡ ካርታ ።

በመዠመሪያ ፡ የዓረብን ፡ አገር ፡ ያስገበረው ፡ አክሱማዊው ፡ ንጉሥ ፡ በትክ
ክል ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ በታሪክ ፡ እስካሁን ፡ አልተገለጸም ። በምዕራፍ ፡ ፴፮ ፡ ላይ፡
ኮስማስ ፡ ጽሑፉን ፡ የገለበጠው ፡ በለሐውልት ፡ ንጉሥ ፡ ዓረቢትንና ፡ ኪንዳ ፡ ክል
ፒት ፡ የተባሉትን ፡ ከሌው ፡ ከሜ ፡ ወደብ ፡ ተነሥተው ፡ ከዓረብ ፡ ሳባውያን ፡ ተዋ
ግተው ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አገሩን ፡ የኔ ፡ ሠራዊት ፡ ያዙት ፡ የሚለው ፡ ስለአፌላስ፡
ይሁን ፡ ወይም ፡ ስለሌላ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ አልገለጸም ። ከንግግሩ ፡ በላይ ፡ ስሙ
ሊገኝበት ፡ የሚቻለው ፡ ሐውልታዊ ፡ ሥፍራ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ መሰባበሩን ፡ ባለ
ፈው ፡ አመልክተናል ። በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተነሡት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግላጸር ፤ ሐለቪ ፤
አርኖ ፤ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ሪክማን ፡ ሌሎችም ፡ የዓረብን ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ ከአክሱም ፡
መንግሥት ፡ ጋር ፡ ያለውንም ፡ የፖለቲክና ፡ የሥን ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪካዊ ፡ ግንኙነት ፡
የሚመረምሩት ፡ ሁሉ ፡ ከደቡብ ፡ ዓረብ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ የመጡት ፡ የሳባውያን ፡
ዘር ፡ እዚያ ፡ ለቀሩት ፡ የሳባ ፡ ነገሥታት ፡ ይገብሩ ፡ እንደነበረ ፤ ከዚያም ፡ ከነዚ
ህም ፡ እየተመረጠ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግብር ፡ እያስወጣ ፡ ለነዚያ ፡ የሚልከው ፡ «ነጋሢ
ወይም ፡ ነገሥት ፡ «ትርጓሜው ፡ በሳባውያን ፡ ቋንቋ» ፡ አስገባሪ ፡ ወይም ፡ አስገባሪ
ዎች» ፡ እንደሚባል ፡ ይገልጹሉ ። አስገባሪ ፡ ማለትም ፡ ግብር ፡ አስወጭ ፡ ከማለት ፡
ልዩነት ፡ የለውም ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ሲኖር ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ የመጡት ፡ ኃይልና፡
ጉልበት ፡ ሲሰማቸው ፡ ለነዚያ ፡ መገበርን ፡ አቋርጠው ፡ ሊወጉዋቸው ፡ የመጡት
ንም ፡ እያሸነፉ ፡ መመለሳቸው ፡ በመጨረሻም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ገዥዎቻቸው ፡ የነበ
ሩትን ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ወገኖቻቸው ፡ የሆኑትን ፡ እነዚህኑ ፡ የደቡብ ፡ ዓረቦችን ፡
(ሳባዎችንና ፡ ሂሚያሪትን ፤ ራይዳንን - ሀበሳትን) ፡ መልሰው ፡ ወግተው ፡ ለአክሱም
መንግሥት ፡ ገባር ፡ እንዳደረጉዋቸው ፡ በዚህ ፡ በያዝነው ፡ የታሪክ ፡ ምርመራ ፡ ዘመን፡
በየታሪኩ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ በመጀመሪያ ፡ የአክሱምን ፡ ነፃ ፡ መንግሥትነት ፡ ያቋቋመው ፡
ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ የቀድሞውን ፡ «የነጋሢ-አስገባሪ» ፡ ስም ፡ ይዞ ፡
የነገሠው ፡ ስሙ ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ መሆኑ ፡ በታ
ሪክ ፡ እንደማይታወቅ ፡ ባለፈው ፡ ጠቅሰነዋል ። እንደዚሁም ፡ የራሱን ፡ መንግሥት ፡
ከአቋቋመ ፡ በኋላ ፡ በመርከብ ፡ ተሻግሮ ፡ ወገኖቹን ፡ (የደቡብ ፡ ዓረቦችን) ፡ ሳባው
ያንን ፡ የወረረና ፡ ያስገበረ ፡ ንጉሥ ፡ የትኛው ፡ መሆኑ ፡ እንደዚያው ፡ እንዳለፈው፡
በትክክል ፡ አልታወቀም ።

በዓረብ ፡ አገር ፡ ሊቃውንቱ ፡ ታሪክ ፡ ሲፈላለጉ ፡ ገደረት ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡
የኢትዮጵያ ፡ (አክሱም) ፡ ንጉሥ ፡ በመርከብ ፡ ተሻግሮ ፡ የዓረብን ፡ አገር ፡ ተዋግቶ፡
ማሸነፉን ፡ ይጠቅሳሉ ። ይኸውም ፡ ንጉሥ ፡ በምዕራፍ ፡ ፴፫ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፸ ፡ በነ
ገሥታት ዝርዝር ፡ በB ፡ ፊደል ፡ ተርታ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ላይ ፡ የተመደበው ፡
ዘግዱር ፡ የተባለው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ተብሎ ፡ ከስሙ ፡ መቃረብ ፡ በቀር ፡
ማስረጃ ፡ የሌለው ፡ ግምት ፡ ተሰጥቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ገደረት ፡ የተባለ ፡
ንጉሥ ፡ መዋጋቱና ፡ ለጊዜው ፡ ማሸነፉ ፡ እርግጥ ፡ ሲሆን ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡

ተሸንፏልና ፡ ለዘለቄታ ፡ ያስገበረ ፡ እርሱ ፡ አይደለም ፡ በማለት ፡ የዓረብን ፡ አገር ፡ በመገመሪያ ፡ ለአክሱም ፡ መንግሥት ፡ ያስገበረ ፡ በ፴፮ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ያመለከትነው ፡ አፊላስ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ሲሉ ፡ መርማሪዎች ፡ ከአንድ ፡ አወላዋይ ፡ ፍርድ ፡ ወደሌላ ፡ አወላዋይ ፡ ፍርድ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ከገደረት ፡ ወደአፊላስ ፡ ተላልፈዋል ።

ታልሙድ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ አንድ ፡ ረቢ ፡ የተባለ ፡ እስራኤላዊ ፡ የደቡብ ፡ ዓረብን ፡ በ፻፴ ዓ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ በጐበኘ ፡ ጊዜ ፡ በዋናው ፡ ከተማ ፡ ደርሶ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ አሠራር ፡ ተመልክቶ ፡ ከደነቀ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡና ፡ እቴጌዪቱ ፡ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ዓረቦች ፡ ሳይቀላ ፡ ጠያይም ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ ከሸማግሌዎች ፡ ጠይቆ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ የዓረብን ፡ አገር ፡ ለመግዛት ፡ የመጡ ፡ የኩሽ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ማግኘቱን ፡ የዛሬ ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ ይጠቅሰዋል ። ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ገጽ ፡ ፻፳ ፡ ተመልከት ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በመላ ፡ አፊላስ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ፫፻ኛው ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ያለ ፡ አክሱማዊ ፡ ንጉሥ ፡ በተረጋገጠ ፡ አኳኋን ፡ የደቡብን ፡ ዓረብ ፡ ካስገበረ ፡ ወዲህ ፡ ቀድሞ ፡ የአክሱምና ፡ የዙሪያው ፡ ከተሞች ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ ከተሞች ፡ ከዛፋርና ፡ ከሌሎችም ፡ ጋር ፡ ሸቀጥ ፡ ለሸቀጥ ፡ ይነጋገዱበት ፡ የነበሩት ፡ ቀረና ፡ አሁን ፡ በትክክል ፡ ዓረብ ፡ ለአክሱም ፡ ገባር ፡ ሆነ ። ባለፈው ፡ በ፴፱ነኛውና ፡ በ፵ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ በ፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ዒዛና ፡ (አብርሃ ፡) የአክሱም ፡ የሳባ ፡ የሐበሳት ፡ የረይዳን . . . . . ፡ ንጉሥ ፡ እያለ ፡ ለአክሱም ፡ ተገዥ ፡ የሆኑትን ፡ የዓረብን ፡ አገሮች ፡ እየዘረዘረ ፡ ይጠራብቸው ፡ እንደነበረ ፡ አንብበናል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብርሃ ፡ ካለፈና ፡ አፄ ፡ ካሌብ ፡ በነገሠበት ፡ መካከል ፡ የዓረብ ፡ አገር ፡ ከአክሱም ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ ነፃነቱን ፡ ይዞ ፡ የተቀመጠ ፡ ይመስላል ፡ የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ አብርሃ ፡ እንደርሱ ፡ የመሰለ ፡ ገናና ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ በዙፋኑ ፡ ሳይከተለው ፡ ስለቀረ ፡ የተከታዩን ፡ ደካማነት ፡ በመጠቀም ፡ ዓረቦቹ ፡ ወይም ፡ ከያለበት ፡ የተጠራቀሙት ፡ አይሁዶች ፡ ነፃነታቸውን ፡ ይዘው ፡ ይሆናል ።

በዚሁም ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ ይልቁንም ፡ በየመን ፡ በየጊዜው ፡ በፓለስቲን ፡ በተደረገው ፡ ጦርነትና ፡ ስደት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ የአይሁድ ፡ ተወላጆች ፡ አገራቸውን ፡ ፓለስቲንን ፡ እየተዉ ፡ በየመን ፡ ተቀምጠዋል ። የአሶርና ፡ የባቢሎን ፡ ነገሥታት ፡ የናቡከደነጾር ፡ ጦር ፡ በምዕ ፡ ፲፱ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በያለበት ፡ ከበታተናቸው ፡ ወዲህ ፡ በሮማውያን ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በተለይ ፡ ከኔሮን ፡ ዘመን ፡ ዠምረው ፡ አይ

ሁዶች ፡ ከሮማውያን ፡ መንግሥት ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ ሸፍተው ፡ ስለነበረ ፡ ቬስባስያኖስና ፡ ይልቁንም ፡ ልጁ ፡ ጢጦስ ፡ (ቲቱስ፡) ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ አስ ጨንቀው ፡ አስገበሩዋቸው ። በዚህ ፡ ጦርነት ፡ በጢጦስ ፡ የሚመራው ፡ የሮማ፡ ወታደር ፡ በእስራኤሎች ፡ ላይ ፡ በመፍጀትና ፡ በማሰቃየት ፡ ብዙ ፡ የጭከኔ ፡ ሥራ ፡ ፈጸመባቸው ። ይኸም ፡ የሆነው ፡ ከክርስቶስ ፤ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፸ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ባለፈው ፡ በጢጦስ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ ጠቅሰነዋል።

ከዚህ ፡ ሥቃይና ፡ ሞት ፡ ያመለጡት ፡ ይሁዲዎች ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ ቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ ወገኖቻቸው ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ ተቀመጡ ። በዘመን ፡ ብዛትም ፡ በርክተው ፡ መንግሥት ፡ አቁመው ፡ ለራሳቸው ፡ ንጉሥ ፡ እያነገሡ ፡ መተዳደር ፡ ከገመሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኗቸው ፡ ባሁኑ ፡ በአፄ ፡ ካሌብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፬፻፹፩–፭፻፲፩ ፡ ዓ፡ ም፡ የነበረው ፡ ንጉሣቸው ፡ የኛ፡ ጽሑፍ ፡ ፊንሐስ ፡ የላቲንና ፡ የዓረብ ፡ የፋርስ ፡ ጸሐፊ ፡ ድሁ ፡ ኖቫስ ፡ ዱና እን–ዲምኖ–ዱናስ ፡ ይለዋል ።

ከዐረብ ፡ አገር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፤ የሚገኘው ፡ የፋርስ፡መንግሥት ፡ ገና፡ ከመዠመሪያ ፡ ዠምሮ ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በሮማ ፡ መንግሥት ፡ እየተመታ ፡ ሲገብር ፡ አልገብርም ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋ ፡ የሮማን ፡ ወታደር ፡ የመ ከተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ፋርስንም ፡ ለማስገበር ፡ ብዙ ፡ የሮማ ፡ ነገሥታት ፡ ሞክ ረው ፡ በፍጹም ፡ የማይቻላቸው ፡ ሆኗል ። በዚሁም ፡ ቫሌርያኖስ ፡ የሚባለው ፡ ፪፻ ፶፬–፪፻፷ ፡ ዓ፡ ም፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ቄሣር ፡ ከፋርሶች ፡ ሲዋጋ ፡ ተማርኮ ፡ መገደ ሉን ፤ የክርስቲያን ፡ ጠላት ፡ የነበረው ፡ ዩልያኖስ ፡ የሚባለው ፡ ፫፻፷፩–፫፻፷፫ ፡ ዓ፡ ም ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ቄሣር ፡ ከፋርሶች ፡ ሲዋጋ፡ ባንድ ፡ የፋርስ ፡ ወታደር ፡ ጦር፡ ተዋግቶ ፡ መውደቁን ፡ ከወደቀም ፡ በኋላ ፡ «ገሊላዊ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡ አሸነፍኸኝ»፡ ብሎ ፡ ከጮኸ ፡ በኋላ ፡ መሞቱን ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። ስለዚህ ፡ ጥንት፡ ከሮማውያን ፡ እየሸሹ ፡ በየመን ፡ መጥተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ እማቆም ፡ የደረ ሱት ፡ አይሁዶች ፡ ጥንት ፡ ላባቶቻቸውም ፡ ለነርሱም ፡ ጠላት ፡ የሆነው ፡ ፋርስ ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ከሮማ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ጠበኛ ፡ በመሆኑ፡አይ ሁዶቹ ፡ የፋርስን ፡ መንግሥት ፡ ጥገኛና ፡ ወዳጅ ፡ አደረጉት ። በሃይማኖት ፡ ምንም፡ እንኳን ፡ የኦሪትና ፡ የዞሮአስትር ፡ እምነት ፡ ቢለያይ ፡ የዚሁ ፡ የፖለቲካውና፡የጦ ርነቱ ፡ ዝንባሌ ፡ የሮማውያን ፡ ጠላትነት ፡ አይሁድንና ፡ ፋርሶቹን ፡ ባንድነት ፡ በወ ዳጅነት ፡ እንዲያብሩ ፡ አደረጋቸው ።

እንደዚሁም ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ የ፬ኛውና ፡ የ፭ኛው ፡ የ፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ቄሣሮች ፡ ግማሾቹ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይን ፡ የሚያምኑ ፡ በዚ ህም ፡ በቁስጥንጥንያ ፡ ነገሥታትና ፤ ለአክሱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ነገሥታት፡ የሃይማኖት ፡ አባት ፡ ከሆኑት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ጠብ ፡ ቢኖርም ፡ ዘሮ ፡ ዘሮ ፡ ያው ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆናቸው ፡ የፋርስና ፡ የአይሁድ ፡ አንድነት ፡ የቁስጥንጥንያንና ፡ የአክሱምን ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥታት ፡ ባንድነት፡

እንዲያብሩ ፡ ሃይማኖትና ፡ ፖለቲክ ፡ ተጣምሮ ፡ ሁለቱ ፡ ባንድነት ፡ እንዲሰለፉ ፡ አደረጋቸው ። አይሁድ ፡ በዐረብ ፡ አገር በበረከተው ፡ ዓይነት ፡ ክርስቲያንም ፡ በዚያው ፡ በጕኑ ፡ እየበረከተ ፡ ሲሄድ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በጠብ ፡ ዓይን ፡ መተያየት ፡ ዠመሩ ። አይሁዶቹን ፡ ፋርስ ፡ ሲደግፍ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ የቍስጥንጥንያና ፡ የአክሱም ፡ መንግሥታት ፡ ይደግፏቸው ፡ ዠመር ። በዐረብ ፡ አገር ፡ ናግራን ፡ ባሉት ፡ ክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በጸሎት ፡ ላይ ፡ የአክሱምና ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ ንጉሥታት ፡ ስም ፡ ማንሣት ፡ የተለመደ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በአክሱም ፡ መንግሥት ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የመሠረተውን ፡ ክርስትና ፡ ፱ኙ ፡ ቅዱሳን ፡ ከቍስጥንጥንያና ፡ ከሶርያ ፡ ከአንጾኪያ ፡ መጥተው ፡ እንዳስፋፉ ፤ እንደዚሁም ፡ ለመዠመሪያ ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ በናግራን ፡ ክርስትናን ፡ የመሠረተው ፡ ፋሚውም ፡ የሚባል ፡ የሶርያ ፡ ተወላጅ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ከዚያም ፡ በየጊዜው ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ ብዙ ፡ መነኰሳት ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ጳውሎስ ፡ ያሉት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ በየጊዜው ፡ እየሄዱ ፡ ክርስትናን ፡ አስፋፉ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ የዐረብ ፡ አገር ፡ የደቡብ ፡ ክፍል ፡ እንደዛሬው ፡ የመንና ፡ ሔጃዝ ፡ ተብሎ ፡ በሁለት ፡ ስም ፡ በሁለት ፡ መንግሥት ፡ በመጠራት ፡ ፈንታ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የታወቁ ፡ ሂሚያሪት ፤ ሳባ ፤ ካታባን ፡ ሐድራሞት ፤ ሂራ ፤ የሚባሉ ፡ ሌሎችም ፡ እየተለዩም ፡ እየተደበለቁም ፡ የሚኖሩ ፡ ነገዶች ፡ ነበሩበት። በነዚህ ፡ ውስጥም ፡ ብዙ ፡ አውራጃዎች ፡ ነበሩ ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የአክሱም ፡ ግዛት ፡ የነበሩትን ፡ ሕሜር ፡ (ሂሚያሪት) ፤ ራይዳን ፤ ሳባ ፤ ሳልሔን ፤ . . . . ፡ እያለ ፡ የአብርሃ ፡ (ዒዛና) ፡ ሐውልት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደጠቀሳቸው ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በአብርሃና ፡ በካሌብ ፡ መካከል ፡ ፩፻፶ ፡ ዓመት ፡ የሚያህል ፡ ጊዜ ፡ ሲኖር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ የዐረብ ፡ አገር ፡ ግዛቶቹን ፡ በቅርብ ፡ መቆጣጠር ፡ ሳይችል ፡ የለቀቀው ፡ ወይም ፡ ችላ ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በፖለቲክና ፡ በአስተዳደር ፡ ሲለያዩ ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ ይልቁንም ፡ የናግራኖቹ ፡ የአክሱምን ፡ መንግሥት ፡ እንደበላይ ፡ ጠባቂና ፡ ደጋፊ ፡ መቁጠራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በደቡብ ፡ ዐረብ ፡ ይልቁንም ፡ በሀገረ ፡ ናግራን ፡ የአክሱምና ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥታት ፡ በሩቅ ፡ ስለሚገኙ ፡ አይሁዶቹና ፡ አረማውያኑ ፡ ተባብረው ፡ እያደር ፡ በጠብ ፡ ዓይን ፡ እያዩ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ በየጊዜው ፡ እያጠቁ ፡ ከማጥቃትም ፡ አልፈው ፡ ይፈጁዋቸው ፡ ዠመር ። የፍጅቱንና ፤ የእልቂቱን ፡ ዓይነት ፡ ክርስቲያኖቹንም ፡ ለመበቀል ፡ የአክሱም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ካሌብ ፡ የተጓዘበትን ፡ ጕዞና ፡ ድል ፡ ከደረገ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ከተበቀለ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞውን ፡ ግዛት ፡ እንደገና ፡ አደላድሎ ፡ ወደአክሱም ፡ መመለሱን ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመለከታለን ።